# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት | ቁጥር 053 | ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም | ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



## ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ








ፎቶ፡- በወልደ ገ/ጊ

# "አፍሪካ አሁን የሆነችውን ብቻ ሳይሆን ያላትን አቅም አገናዝበው ልትሆን የሚገባትን የሚቀምሩላት ወጣት ልጆቿ ናቸው"

\- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

- ለቀድሞ የፓን-አፍሪካን መሪዎች ሽልማት ተበርክቷል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ አሁን የሆነችውን ብቻ ሳይሆን ያላትን አቅም አገናዝበው ልትሆን የሚገባትን የሚቀምሩላት ወጣት መሪዎቿ ናቸው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ፡፡ ከጥቅምት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የነበረው የአፍሪካ ወጣት መሪዎች ጉባኤ ትናንት ተጠናቋል፡፡ በማጠቃለያው መርሃግብርም ለአፍሪካ አንድነትና ፓን አፍሪካኒዝም አስተዋጽኦ ላደረጉ 17 የአፍሪካ አገራት የቀድሞ መሪዎች ሽልማት ተበርክቷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለአራት ቀናት ሲካሄድ የቆየውን የአፍሪካ ወጣት መሪዎች ጉባዔ ማጠቃለያ መርሐ ግብር ላይ እንደተናገሩት፥ በአፍሪካ ምድር ብዙ

"አፍሪካ አሁን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከአሸባሪው ትህነግ ነጻ በወጡ የትግራይ አካባቢዎች የሰብዓዊ አቅርቦቶችን ለማድረስ እየሰራ መሆኑን ቢሮው አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በተቆጣጠራቸው የትግራይ ክልል አካባቢዎች የሰብዓዊ አቅርቦቶችን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ እርዳታ ማስተባበሪያ ቢሮ (ኦቻ) አስታውቋል።

በኢትዮጵያ የማስተባበሪያ ቢሮው ዳይሬክተር ሚሼል ሳድ እንደገለጹት፤ መንግሥት በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች የሰብዓዊ አቅርቦቶችን ተደራሽ ለማድረግ የጀመረው ጥረትና ለሰብዓዊ ድርጅቶች ያቀረበው ጥሪ

ከአሸባሪው ትህነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የኢትዮጵያ ቀጣይ ጊዜ ሰላም እንዲሆን አሸባሪው ሕወሓት ትጥቅ መፍታት አለበት

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መጪው ጊዜ ሰላም እንዲሆን አሸባሪው ሕወሓት ትጥቅ መፍታት እንዳለበት የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን) አሳሰበ።

በአፍሪካ ሕብረት አስተባባሪነት በመንግሥትና በአሸባሪው ሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ እየተካሄደ የሚገኘው የሰላም ንግግር የሽብር ቡድኑን ድርጅታዊ ህልውና ባከሰመ መንገድ መካሄድ እንዳለበትም አብን

የኢትዮጵያ ቀጣይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ሃዲስ አብርሃ

ዶክተር መለስ መኮንን

# ኢትዮጵያ ለስንዴ ግዥ በዓመት የምታወጣውን አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጪ ማስቀረት ተችሏል

\- ከመኸር እርሻው 108 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ይጠበቃል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የስንዴ ምርታማነት ላይ ትኩረት በመደረጉ ኢትዮጵያ በዓመት ለስንዴ ግዥ የምታወጣውን አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጪ ማስቀረት መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። ከመኸር እርሻው 108 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅም ጠቁሟል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን ትናንትና በሰጡት መግለጫ ፤ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ700 ሚሊዮን እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ለስንዴ ግዥ ታወጣ ነበር፤ አሁን ላይ ምርት በበቂ ሁኔታ በመዘጋጀቱ ወጪው አይኖርም ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለስንዴ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
## ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


## ሕወሓት በአማራ ክልል በጦርነቱ ምንም አይነት ተሳትፎ የሌላቸው 7 ሺህ 3 ሰዎችን ገድሏል

- ከ 837 ሺህ በላይ የቤተሰብ አባላት ላይ ልዩ ልዩ ጉዳቶችን አድርሷል

ገጽ 3

# የልማት ተነሺ አርሶአደሮችን ተስፋ ያስመለሰው ማዕከል

**ሞገስ ተስፋ**

በአዲስ አበባ ከተማ መስፋፋት ምክንያት ከይዞታቸው የተፈናቀሉ አርሶአደሮች ተጠቃሚ አለመሆናቸው ባለፉት ዓመታት በሰፊው ሲነሳ የቆየ ጉዳይ ነው። አርሶአደሮቹ ከመሬታቸው ያለበቂ የካሳ ክፍያ በልማት ሲፈናቀሉ እንደነበር በተለያየ ጊዜ የሚነሳ ጥያቄ ነበር። ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ ከልማት የተነሱት አርሶ አደሮች የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከተማ አስተዳደሩ ሰፊ ስራ እየሰራ ነው። ከሰሞኑ ከተማ አስተዳደሩ ከአጋር አካላት ጋር እያስገነባቸው ካሉት ሜጋ ፕሮጀክቶች መካከል ኮየፈቼ የሚገኘው የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች የእንስሳት እርባታና ተዋጽኦ ማዕከል አንዱ ነው።

ማዕከሉ የልማት ተነሺ አርሶአደሮችን በአነስተኛ መሬት ራሳቸውንና ቤተሰባቸው ቀይረው ለማህበረሰቡ ግብዓት ለማቅረብ የሚያስችል ነው ተብሏል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር አያልነሽ ሃብተማሪያም ባለፈው ሳምንት የመገናኛ ብዙሃን የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ያሉበትን ሁኔታ በጎበኙበት ወቅት እንደገለጹት፤ በከተማ አስተዳደሩ በርካታ የሆኑ ለህብረተሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እየተገነቡ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ መስፋፋት ምክንያት የልማት ተነሺ የሆኑ ከ2 ሺ በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮችን ከእነ ቤተሰቦቻቸው ተጠቃሚ የሚያደርግ የልማት ተነሽ




የእንስሳት እርባታና ተዋጽኦ ማዕከል አንዱ መሆኑን ኢንጂነሯ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ በ 14 ሺ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሲሆን ሶስት መቶ ከብቶችን የሚያደልብ፣ በቀን 20 ሺ ሊትር ወትት የሚያስገኙ ሶስት መቶ የወተት ላሞችን የሚይዝ እያንዳንዱ 10 ብሎኮች ያሉት ነው። በተጨማሪም 300 ኪዩቢክ ውሃ መያዝ የሚችል ሪዘርቫየር ያለው ሲሆን 40ሺ ዶሮዎችን በማርባት በአንድ ጊዜ 30 ሺ እንቁላል ያስገኛሉ፤ እንዲሁም የምርት መሸጫና ማሳያ የሚሆኑ 32 መጋዘኖችና ጤና ጣቢያ ያለው ነው። ይህም ለከተማ አስተዳደሩ ማህበረሰብ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ኢነጂነር አያልነሽ ተናግረዋል። ከሚደልቡ ከብቶች ከእንዳንዳቸው 350 ኪሎግራም ስጋ የሚያስገኝ ነው። ከሁሉም ጋር ተዳምሮ ለከተማውና ለአካባቢው ማህበረሰብ የእንስሳት ተዋጽኦ ማስገኘት የሚችል ነው። ግንባታውም 90 በመቶ ተጠናቋል።

ኢንጂነር አያልነሽ፤ የእንስሳት ተዋጽኦ ትስስር በመፍጠር የዶሮ ተረፈ ምርትን ለማዳበሪያና ለአሳ ምግብነት እንዲውል በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ነው። ውስን የሆነ የውሃ ሀብትን ላለመሻማት የከርሰ ምድር ውሃን በማዘጋጀት ለከብቶች ለመጠጥም ሆነ ለጽዳት የከርሰ ምድር ውሃን መጠቀም የሚያስችል ነው። በተጨማሪም በአካባቢው ምቹ የሆነ ከባቢ ከመፍጠር አንጻር አረንጓዴ የማልበስ ስራ የተሰራበት ነው። ይህም ለአርሶ አደሮቹ ምቹና ተስማሚ የስራ አካባቢ እንዲፈጠር ያደረገ ነው ያሉት።

ኢንጂነር አያልነሽ፤ ማዕከሉ በልማት ተነሽ የሆኑ አርሶ አደሮች የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው። አለፍ ሲልም የአዲስ አበባ ከተማ ማህበረሰብ ከአርሶ አደሮቹ ከሚገኝ የእንስሳት ተዋጽኦ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የተፈጠረበት በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ነው ብለዋል።

ከሁለት ሺ በላይ የልማት ተነሽ አርሶአደሮችን ተስፋ ያለመለመው የእንስሳት ተዋጽኦ ማዕከል ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። የልማት ተነሽ አርሶ አደሮችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ ግንባታው እየተፋጠነ ያለው ማዕከሉ ባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ላይ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን አሁን ለማጠናቀቅ ውስን ስራዎች ቀርተውታል።

አዲስ አበባ የአፍሪካና ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መቀመጫነቷን የሚመጥኑ ከአምስት በላይ የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ናቸው።




# የትግራይ ተወላጆች አሸባሪው ሕወሓት በአገር ላይ ያደረሰውን ጥፋት በሰላማዊ ሰልፍ አወገዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኮምቦልቻ ከተማ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች አሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ ጦርነት በመክፈት በንጹሃን ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና የውጭ ጣልቃ ገብነትን የሚያወግዝ ሰላማዊ ሰልፍ አካሄዱ።

ከሰልፉ አስተባባሪዎች መካከል አቶ ገብረሕይወት አየለ ለኢዜአ እንዳሉት፣ ሰልፉ አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍና መከራ ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅ ያለመ ነው። በተጨማሪም የትግራይ ክልል ሕዝብ በሀገር መከላከያ ሠራዊት ተጋድሎ ከሽብር ቡድኑ ጫና ነጻ እንዳይወጣ አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ የሚያደርጉትን ጣልቃ ገብነት እንዲያቆሙ ለመጠየቅም ጭምር ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ዕድሜያቸው ያልደረሱ ሕጻናትን አስገድዶ ወደ ጦርነት በማሰለፍ እየፈጸመ ያለው ወንጀልና የሰብዓዊ መብት ጥሰት በአስቸኳይ ማቆም እንዳለበት ለማስገንዘብ ያደረጉት ሰልፍ መሆኑንም አስረድተዋል።

“እኛ የትግራይ ክልል ተወላጆች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ጋር አንድነታችንን ጠብቀን የአገራችንን ሉዓላዊነት በጋራ መጠበቅ እንፈልጋለን” ሲሉም አስተባባሪው ገልጸዋል።

ሰልፈኞቹ “አሸባሪው ሕወሓት የትግራይ ክልል ሕዝብን አይወክልም!” ፣ “ለጥቂት ሥልጣን ፈላጊዎች ሲባል የትግራይ ወጣት የጥይት ሰለባ መሆኑ ይብቃ!” ፣ “የሽብር ቡድኑ የትግራይ ሕዝብም ጠላት ነው!” የሚሉ መፎክሮችንም አሰምተዋል።

በተጨማሪም “በድርድር ስም የሕወሓትን ዕድሜ ማራዘም ይብቃ!”፣ መንግሥት የጀመረውን ሕግ ማስከበር አጠናክሮ የትግራይ ክልል ሕዝብን ነጻ ማውጣት አለበት!”፣ መከላከያ ሠራዊት የነጻነታችን ዓርማ የአንድነታችን ዋልታ ነው!” ፣ ከመከላከያ ሠራዊት ጎን እንቆማለን!” የሚሉና ሌሎች መልዕክቶችም በሰልፉ ተሳታፊዎች ተላልፈዋል።

ሰልፈኞቹ ከኢትዮጵያውያን ወንድምና እህቶቻቸው ጋር በአንድነት ሰላማቸውን ጠብቀው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እንደሚያስቀጥሉም በሰልፉ ላይ አረጋግጠዋል።

ጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትን ከመደገፍ ባለፈ የሽብር ቡድኑ የከፈተውን ጦርነት በጋራ ለመመከት ዝግጁ መሆናቸውንም ሰልፈኞቹ ገልጸዋል።

የትግራይ ክልል ሕዝብ በአሸባሪው ሕወሓት እየደረሰበት ያለው እንግልትና ስቃይ እንዲያበቃ ሁሉም ሊረባረብ እንደሚገባ የጠየቁት ሰልፈኞቹ፣ ለሕዝብ የመጣን እርዳታ ዘርፎ በመውሰድ ሕዝብን ለችግር ያጋለጠን አሸባሪውን ሕወሓት ማጥፋት እንደሚገባ ተናግረዋል።

በኮምቦልቻ ከተማ ዋና ዋና መንገዶች እየተካሄደ ያለው ሰላማዊ ሰልፍ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አደባባይ በጋራ በመሰባሰብ መልዕክት ተላልፎበታል።

# አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ ኢትዮጵያን ለውጭ ታሪካዊ ጠላቶች ለመስጠት ነበር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ የግዛት አንድነት አፍርሶ ለውጭ ታሪካዊ ጠላቶች አሳልፎ ለመስጠት ያለመ እንደነበር ተገለጸ።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ለኢዜአ እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ በልጆቿ አርበኝነት ታፍራ እና ነጻነቷን አስከብራ ብትቆይም በየዘመኑ ባንዳ እና ጠላቶች ፈትነዋታል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት የጠላቶችን አጀንዳ ለማስፈጸም እንዲሁም ለራሱ ሥልጣን እና ጥቅም ሕዝብን በተለያዩ ማንነቶች እርስ በርስ ለመከፋፈል ያልፈነቀለው ድንጋይ እንዳልነበር ገልጸዋል።

ቡድኑ ከማዕከላዊ መንበረ ሥልጣኑ በሕዝብ ግፊት ከተወገደ በኋላም ኢትዮጵያን ለጠላት አሳልፎ የመስጠት ባንዳነት ነውሩን እንደቀጠለበት አውስተዋል።

አሸባሪው ቡድን ከ20 ዓመታት በላይ በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ የሀገር ሉዓላዊነትን ሲያስከብር እና የትግራይን ክልል ሕዝብ ሲጠብቅ እና ክልሉን ሲያለማ የቆየው የሰሜን ዕዝ ሠራዊት ላይ ከፈጸመው የክህደት እና የግፍ ጭፍጨፋ ጀርባ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለጠላት ማጋለጥ እና ሀገር የማፍረስ ተልዕኮ ነበረው ብለዋል።

የሰሜን ዕዝ ጭፍጨፋ ጥቁር ጠባሳ ጥሎ ያለፈ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ የጀመረቻቸውን የልማት ውጥኖች ለማሰናከል በታሪካዊ ጠላቶች አይዞህ ባይነት የተፈጸመ ድርጊት መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የጥቁሮች የነጻነት ፋና መሆኗን ያልወደዱ አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራቱን ለማዳከም እና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛትን ለማምጣት አሸባሪውን ሕወሓት እና ባንዳዎችን በትሮይ ፈረስነት ተጠቅመዋል ነው ያሉት።

በዚህም በሰሜን ዕዝ የተፈጸመው ጥቃት በዓለም ከተፈጸሙ አሰቃቂ እና ዘግናኝ ድርጊቶች የከፋ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከ30 ዓመታት በላይ በታንከኛ ክፍል ያገለገሉት ብርጋዲየር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ የጥቅምት 24ቱ ሰሜን ዕዝ ጥቃት በታሪክም መጥፎ ትውስታ ነው ሲሉ አንስተዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በኢትዮጵያ እና በሕዝቧ ላይ የፈጸመው ግፍ እና በደል በየትኛውም መንገድ የማይሻር ጠባሳ መሆኑን ገልጸዋል።


ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን


ብርጋዲየር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ

ቡድኑ የኢትዮጵያ የሉዓላዊነት ምሽግ የሆነውን የመከላከያ ሠራዊት ከጀርባ በመውጋት የፈጸመው ጭፍጨፋ ግቡ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ የግዛት አንድነት በመጣስ ሀገርን በታትኖ ለጠላት ለመስጠት መሆኑን አንስተዋል።

አስተያየት ሰጪዎቹ በሰሜን ዕዝ ጭፍጨፋ ለተሰው የኢትዮጵያ ወታደሮች መታሰቢያ ማቆም፣ ለሠራዊት ቤተሰቦችም ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ማድረግ ከመንግሥትና ከሕዝቡ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

ብርጋዲየር ጄኔራል ዋሲሁን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ጠላትና ባንዳ ቢፈራረቁባትም በጀግኖች ልጆቿ መሥዕዋትነት ፀንታ ትቀጥላለች። ለሀገሩ ክብር እና ሉዓላዊነት የህይወት መሥዕዋትነት ለሚከፍለው ጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊትም ዕውቅና መስጠት መጀመሩ ሌሎች ጀግኖችን ለማፍራት ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡

# ከሥርዓተ ትምህርቱ ውጪ የሚሰሩ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ ባለሥልጣኑ አስታወቀ


ወይዘሮ ሕይወት ጉግሳ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ትምህርትና ሥልጠና ቁጥጥር ባለሥልጣን ከአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ውጪ ያልተጠናና መንግሥት ያልፈቀደው የትምህርት ሥርዓትን የሚከተሉ እንዲሁም ተማሪዎች ከትምህርት ሂደቱ ጋር የማይገናኙ ቁሳቁስ እንዲያመጡ የሚያስገድዱ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ በአፍ መፍቻ ቋንቋና በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ የፓናል ውይይት ተካሂዷል። በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ የአዲስ አበባ የትምህርትና ሥልጠና ቁጥጥር ባለሥልጣን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት በውይይቱ ተገኝተዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርትና ሥልጠና ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሕይወት ጉግሳ በውይይቱ እንደተናገሩት፤ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በተመለከተ የትምህርት ክትትልና ጥራት ፍተሻ እየተደረገ ነው። በዚህም መንግሥት ያልፈቀደውና ከአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ውጪ የትምህርት ሥርዓትን የሚከተሉ የትምህርት ተቋማት እንዳሉ በጥናት ተረጋግጧል።

ተቋማቱ መንግሥት ያስቀመጠውን የትምህርት ሥርዓት እንዲከተሉ መልዕክት በማስተላለፍ ከዚህ ድርጊት የማይቆጠብ ተቋም ካለ በተቀመጠው ሕግና ደንብ መሰረት በቶሎ እርምጃ እንደሚወሰድ ተናግረዋል።

በትምህርት ተቋማቱ ከተገኙት የአሰራር ችግሮች ውስጥ አንደኛው ከሌሎች ሀገራት የተቀዱ ሥርዓተ ትምህርትን በሀገሪቱ የሥርዓተ ትምህርት መመዘኛ መስፈርቶች ሳይጠና ተማሪዎች እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው። ይህም ተማሪዎች ከሀገር ውስጥ ባህል፣ ሥነ ሥርዓትና ጥበብ ጋር እንዲራራቁ በማድረግ በውጭ ሀገራት ባህል የሚማረክ ትውልድ እንዲፈጠር ያደርጋል።

ሁለተኛ ተማሪዎች በተገቢው ሰዓት መማር ያለባቸውን የትምህርት አይነት በሌሎች የትምህርት አይነቶችን እንዲተኩ ማድረግ ሲሆን ይህም ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል። ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ ተደራራቢ የትምህርት ጫና ነው። ጉዳቱም ተማሪዎች ለጭንቀት እንዲዳረጉ ያደርጋል ብለዋል።

ሶስተኛ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር በተያያዘ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል በሀገር ውስጥ ቋንቋ መማር ያለባቸውን ትምህርቶች በእንግሊዝኛ እንዲማሩ የሚያደርጉ የግል ትምህርት ቤቶች አሉ ያሉት ወይዘሮ ሕይወት፤ በሀገሪቷ በአፍ ቋንቋ የመማር መብትን የሚፃረር በመሆኑ ተቋማቱ ከወዲሁ መፍትሄ እንዲያበጁ አሳስበዋል።

እንደ ወይዘሮ ሕይወት ገለፃ፤ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎች ሀገራቸውን እንዲያውቁ፣ እንዲደግፉና ሀገራዊ አስተሳሰብ ይዘው እንዲያድጉ ተደርጎ የተቀረፀ ነው። በዚህም በርካታ ምሁራንና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል። እነዚህ አካላት ያልተሳተፉበትን የትምህርት ሥርዓት ለተማሪዎች ማስተማር ሀገርን ከማሳደግ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል።

ይህም ልጆች ከፍ እያሉ ሲሄዱ ትምህርት እንዲጠሉ ከማድረግ ባለፈ ልጆች ተገቢውን የሀገር ፍቅር እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል ያሉት ወይዘሮ ሕይወት፤ ይህን በሚፈጽሙ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።

በአዲስ አበባ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጠንካራ ቅድመ ዝግጅት መደረጉን የተናገሩት ሥራ አስኪያጇ፤ በዝግጅቱ የሀገሪቷን የትምህርት ፖሊሲን የሚመጥን የመማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል።

በዚህም 3 ነጥብ 9 ሚሊዮን መጽሐፍት በኮፒ የተዘጋጀ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን የሚሆነው ተሰራጭቷል። መጽሐፉ ያልደረሳቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሶፍት ኮፒ እንዲያገኙ በማድረግ ትምህርት እንዲጀምሩ ተደርጓል ብለዋል።

አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተግባር ላይ ከመዋሉ በፊት 44 አንደኛና በሁለተኛ ትምህርት ቤቶች ላይ የትግበራ ሙከራ መደረጉን ጠቁመው፤ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በተመለከተ ባለሥልጣኑ ጠንካራ የትምህርት ክትትልና ጥራት ፍተሻ እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

---

# የአፍሪካ የፋሽን አውደርዕይ በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው

## -ከኢትዮጵያ 39 አምራቾች ይሳተፋሉ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- 8ኛው የአፍሪካ ሶርሲንግና የፋሽን ሳምንት (ASFW) በሚል ከጥቅምት 25 እስከ 28 ቀን 2015 በአዲስ አበባ አውደርዕይ እንደሚካሄድ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ። በአውደ ርዕዩ ከኢትዮጵያ 39 የጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች እንደሚሳተፉ ተጠቁሟል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ባዛሩን አስመልክቶ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት ከጥቅምት 25 እስከ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ በሚካሄደው 8ተኛው የአፍሪካ ሶርሲንግ እና የፋሽን ሳምንት አውደ ርዕይ ከ30 አገራት የተውጣጡ ከ200 በላይ ዓለም አቀፍ አምራቾችና ላኪዎች ይሳተፋሉ፡፡

አውደ ርዕዩ ከመሴ ፍራንክፈርት ኢግዚቢሽን (GmbH)፣ ከኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳና ልብስ ስፌት ማህበራት ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር የሚካሄድ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአውደርዕዩ ከኢትዮጵያ 39 ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች የሚሳተፉ መሆኑንም ጠቁመው አንጋፋ የአፍሪካ የጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች የሚገኙበት በመሆኑ ለኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል። ከ6000 በላይ የንግድ ባለሙያዎች፣ ግብዓት አቅራቢዎችና ገዢዎች ይጎበኙታል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑንም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ሰፊ የሰው ኃይል ያላት የተለያዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በትኩረት እየተገነቡ እና የአፍሪካ የአምራቾች ማዕከል ለመሆን አቅዳ እየሰራች መሆኑን ያስታወሱት አቶ ታረቀኝ በዛሩም በኢትዮጵያ መካሄዱ የኢንዱስትሪ ማዕከል ለመሆን የራሱ እገዛ አለው ብለዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ100 ሺህ በላይ የስራ እድል መፍጠር ችሏል ያሉት አቶ ታረቀኝ ለወደፊትም መስፋፋት የሚገባው መሆኑን አመላከተዋል።

ኢትዮጵያ አፍሪካን የአምራች ኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ እየሰራች መሆኑን አመላክተው የአፍሪካ የነጻ የንግድ ቀጠናን ማጽደቅ አፍሪካውያን እርስ በርስ ያለንን የንግድ ድርሻ ለማሳደግ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን የንግድ ደረጃ ለማሻሻል ያለመ መሆኑንም ተናግረዋል።

የአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ በመባል የሚታወቀው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሀገር ውስጥ የሚመረተውን ምርት ለመላው ዓለም በማሰራጨት ላይ የተለየ እድል የሚሰጥ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻ የንግድ ቀጠና ማዕከል በድሬዳዋ መመረቁ ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ዕድል መሆኑን አስታውሰዋል። ከኢትዮጵያ ታምርት ጋር ተያይዞ በነበረው መነሳሳት በሀገር ውስጥ ምርት ለመጠቀም መንግሥት በያዘው ቁርጠኝነት ሙሉ ለሙሉ መሳካቱን ጠቁመው በ2014 ሁሉም ዓይነት የሚሊተሪ ዩኒፎርም በሀገር ውስጥ ማምረት ተችሏል ብለዋል።

የጥጥ ምርትን በተመለከተም ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ከውጭ የምታስገባ እንደነበር አስታውሰው በ2014 ዓ.ም 100 በመቶ ኢንዱስትሪዎች የአገር ውስጥ ጥጥ ተጠቅመዋል። ነገር ግን የሀገር ውስጥ የጥጥ ምርት ጥራት ጋር ተያይዞ ቀጣይ ስራ የሚጠይቅ መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህም የውጭ ምንዛሪን ለማስቀረት፣ የስራ እድል ከመፍጠር እና ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ከማምጣት አኳያ ሰፊ ተሞክሮ እና ልምድ የተገኘበት ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና ጋርመንት አምራቾች ማህበር ዋና ጸሐፊ አቶ አገኣዚ ገብረየሱስ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ በምታዘጋጀው በዓለም አቀፍ አውደርዕዩ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት፣ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ፣ የፋሽን ትዕይንትና የፋብሪካ ጉብኝቶችን ያካተተ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

የንግድ ትርኢቱ የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ የንግድ ግንኙነቶችን ለማጠናከርና የገበያ ትስስሮችን ለመፍጠር የጎላ ፋይዳ እንዳለው አመላክተዋል።

በዘርፉ የሚሳተፉ አምራቾችም የጨርቃጨርቅ፣ የአልባሳትና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚያቀርቡ በመሆኑም አምራቾች በሚያገኙት የልምድ ልውውጡ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ይጠበቃል። በዓለም አቀፍ ንግድ ትርኢቱ ሀገር በቀል ኩባንያዎች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ለማስተዋወቅ ያግዛልም ብለዋል።

---

# ሕወሓት በአማራ ክልል በጦርነቱ ምንም አይነት ተሳትፎ የሌላቸው 7 ሺህ 3 ሰዎችን ገድሏል

- ከ 837 ሺህ በላይ የቤተሰብ አባላት ላይ ልዩ ልዩ ጉዳቶችን አድርሷል

**ሞገስ ጸጋዬ**


ዶክተር አስማረ ደጀን

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት በአማራ ክልል በወረራ በቆየበት ወቅት ከሰባት ሺህ ሶስት ንጹሃን ዜጎችን መግደሉን በአማራ ክልል ያሉ የዩኒቨርሲቲዎች ፎረም አስታወቀ፡፤ ቡድኑ ከ837 ሺህ በላይ የቤተሰብ አባላት ላይ የሥነ ልቦና፣ ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳቶች ማድረሱን ባደረገው ጥናት ማረጋገጡን አስታውቋል። ከ291 ቢሊዮን ብር በላይ ንብረትም ማውደሙንም ጠቁሟል።

ሕወሓት በአማራ ክልል በወረራ በቆየበት ጊዜ ያደረሰውን በደል የሚያሳይ «የአማራ ጥላቻና የፈጸመው የዘር ማጥፋት» በሚል ርዕስ የጥናት ውጤት በመጽሐፍ መልክ ታትሞ ለንባብ በቅቷል። መጽሐፉ በአማራ ክልል ያሉ አስር ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም ምሁራንን በማስተባበርና የሚመለከታቸው የፌዴራል ተቋማት ጋር በመሆን የታተመ ነው።

በአማራ ክልል ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም ዋና ጸሀፊ ዶክተር አስማረ ደጀን ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ጥናቱ በጊዜና በቦታ የተገደበ ቢሆንም በርካታ የአማራ አካባቢዎችን ያካለለ ነው።

ዶክተር አስማረ እንደገለጹት፤ ከሰኔ 2013 ዓ.ም ጀምሮ ሕወሓት በአማራ ክልል የፈጸመውን ወረራ እስከተቀለበሰበት ታህሳስ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የነበረውን ጉዳት የያዘ የጥናት ውጤት ነው። ጥናቱ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሲሆን አርባ የሚሆኑ ምሁራን የተሳተፉበት ስራ ነው።

ጥናቱ ሲካሄድ ራያ፣ ሰቆጣ፣ አላማጣ፣ አበርጌሌ፣ አዳርቃይ፣ ማይጠብሪ፣ ወልቃይት፣ ጸገዴ፣ ሰቲት ሁመራን በሕወሓት ቁጥጥር ስለነበሩ አልተካተቱም፤ ሙሉ ለሙሉ ጥናት ቢደረግ ውድመቱ አሁን ካለው በላይ ይሆናል ብለዋል።

አማራ ክልል ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና የውጭ አገር ዜጎች የሚያስተምሩ በመሆኑ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ሁሉ የተካተቱበት በመሆኑ ዓለም አቀፍ መርህን የተከተለ ጥናት መሆኑንም አብራርተዋል።

እንደ ዋና ጸሃፊው ማብራሪያ፤ ጥናቱ ሶስት ዋና ዋና ዓላማ አለው። የወራሪው ኃይል በአማራ ክልል ያደረሰውን ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳት ቆጠራ ማካሄድ፤ የደረሰውን ሰብአዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳቶችን አይነትና ጥልቀት በግለሰብና በተቋማት ደረጃ መለየትና ማደራጀት እንዲሁም የደረሰውን አስከፊ በደልና የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለአገርና ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ ነው ብለዋል። ይህን ይዞ ከታተመው መጽሐፍ ውስጥ 20 የሚሆኑ ጆርናሎችን ለማሳተም ጥረት መጀመሩን ገልጸዋል።

የታተመው መጽሐፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታይ ለማድረግ ወደ እንግሊዝኛ ለማስተርጎም በሂደት ላይ መሆኑን የገለጹት ዶክተሩ፤ የጥናቱ ውጤት እንደሚጠቁመው ሕወሓት በቆይታው የአማራን ብሔር ለማጥፋት የቻለውን ሁሉ ጥረት አድርጓል። ጥናቱ በአማራ ክልል ይሁን እንጂ በአፋር ብሔር ላይም ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።

ቡድኑ በጫካ በነበረበት ጊዜ ጀምሮ አማራን እንደ ጠላት ፈርጆ የተነሳ ቡድን ነው፤ ጥናቱም ያረጋገጠው ያንን በተግባር ማሳየቱን ነው። የተገበራቸውን ጉዳዮች በዝርዝር ስናያቸው የዘር ማጥፋት ፈጽሟል ያስብላል፤ ገምጋሚዎችም ገምግመው አረጋግጠዋል። አሸባሪው ሕወሓት በአማራ ሕዝብ ላይ የፈጸመው በደል ስም የለም እንጂ ከዘር ማጥፋት በላይ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል ብለዋል።

ይፋ ሆነው የጥናት ውጤት ፍቃደኛ ሁነው ምላሻቸውን የሰጡ ተጎጂዎችን የሚመለከት ቢሆንም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሥነልቦና ያልተጎዳ የአማራ ማሕበረሰብ የለም። በመላው ኢትዮጵያውያን ላይም ከፍተኛ የሆነ የሥነ ልቦና ጉዳት ነበር። በዚህም በ837 ሺህ 687 የቤተሰብ አባላት ላይ የሥነ ልቦና ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳቶች ደርሰዋል።

ጥናቱ ሲሰራ የቤት ለቤት ቆጠራ በማድረግ ከ12 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ላይ ደርሰናል። ከነዚህ ውስጥ 409 ሺህ 178 ሴቶች ከፍተኛ ደረጃ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ 263 ሺህ 318 ዜጎች የተስፋ መቁረጥና የመሳሰሉ ጉዳቶች ሰለባ ሆነዋል።

በሰብአዊ ጉዳት ላይ 240 ሺህ 236 ሰዎች ላይ የተለያዩ ጉዳቶች መድረሳቸውን የገለጹት ዶክተሩ፤ ከነዚህም ውስጥ ግድያ፣ ድብደባ፣ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት፣ ተገዶ መደፈር፣ የጉልበት ብዝበዛ፣ ክብረ ነክ ስድቦች፣ ዛቻዎች፣ እገታ፣ አፈናና የጥይት ማብረጃ ማድረግ ናቸው። ከዚህ ውስጥ 29 ሺህ 8 ሰዎች ድብደባ ደርሶባቸዋል፤ 33 ሺህ 537 ሰዎች የጉልበት ብዝበዛ፤ 103 ሺህ 721 ሰዎች ጉንተላና ዛቻ፣ 7 ሺህ 463 ሰዎች አድራሻቸው የጠፋ፣ በጦርነት ምንም ተሳትፎ ሳይኖራቸው 7 ሺህ 3 ሰዎች ተገድለዋል። ከዚህም 1 ሺህ 797 ሰዎች የተረሸኑ፤ 597 ሰዎች በድብደባ የሞቱ፣ 839 ሰዎች ደግሞ በጦርነቱ ምክንያት በመድሃኒት እጦት የሞቱ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

1 ሺህ 939 ሰዎች አስገድዶ መድፈር ደርሶባቸዋል ያሉት ዶክተር አስማረ፤ እናቶች ቤተሰብ ባለበት በቡድን ተደፍረዋል። የካህናት ሚስት በካህናት ፊት ተደፍራለች፤ ወራሪው ቡድን በማስገደድ አባት ልጁን እንዲደፍር አድርገዋል። ቡድኑ ከኢትዮጵያ ወግና ባህል ውጭ በሆነ መልኩ 29 ወንዶች ላይ የግብረሰዶም ተግባር ፈጽሟል።

ቁሳዊ ውድመትን በተመለከተ በአጠቃላይ በ26 የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑና በግል ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ውድመት አድርሷል፤ በተለይ በጤና፣ በግብርና፣ በትምህርትና በመሳሰሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በከፍተኛ ደረጃ ወድመዋል። ይህም በብር ሲሰላ 291 ቢሊዮን 816 ሚሊዮን 377 ሺህ 953 ተመን ያለው መሆኑን በጥናት ተረጋግጧል ብለዋል።

# ድርጅቱ ከ2 ቢሊዮን በላይ ብር የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከሀገር ውስጥ ሊያቀርብ ነው

## - የ18 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ግብዓቶች ከውጭ ሀገራት ይቀርባሉ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት (ኢግልድ) ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከሀገር ውስጥ፤ የ 18 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ግብዓቶችን ከውጭ በማስገባት ለተጠቃሚዎች የሚያቀርብ መሆኑን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ የሺመቤት ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘርፉ የሚታየውን እጥረት ለመቅረፍ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከውጭ እና ከአገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በመሆኑም ድርጅቱ በ2015 በጀት ዓመት በዘርፉ የሚታየውን እጥረት ለመቅረፍ 18 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከውጭ በማስገባት እና 2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥ በመግዛት ለገበያ ለማቅረብ አቅዷል።

ይህንን ዕቅድ ለማሳካት ያመች ዘንድ የሥራ ካፒታልን በማሳደግ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን የማቅረብ አቅምን ለማሳደግ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር ውይይት ተደርጓል ያሉት ወይዘሮ የሺመቤት፤ በቂ የሥራ ካፒታል ባለመኖሩ ባለፈው ዓመት የሚፈለገውን ያህል ግብዓት ማቅረብ ባለመቻሉ ይህን ሁኔታ ለማሻሻል መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ድርጅቱ በከፍተኛ የዋጋ ንረት ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ በትኩረት እየሠራ ነው። ለአብነትም ባለፈው ዓመት ግምቱ 19 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ዘይት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ አድርጓል።

መንግሥታዊ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ትርፉን ከማሳደግ ይልቅ ሕብረተሰቡን በማገልገል ላይ ያተኮረ ነው ያሉት ወይዘሮ የሺመቤት፣ አንዳንዴም በድርጅቱ የሚቀርቡ ምርቶችን ያለምንም ትርፍ እንደሚያከፋፍሉ አብራርተዋል።

ወይዘሮ የሺመቤት፤ ድርጅቱ ከዚህ ቀደም በሚፈለገው ደረጃ ሲያገለግል እንዳልነበርም ተናግረዋል። በድርጅቱ የቀድሞ አመራሮች የመልካም አስተዳደር እጦት እና ሌሎች ችግሮች ተፈጥረው እንደነበር የጠቆሙት ወይዘሮ የሺመቤት ሁኔታው ድርጅቱን ወደ ኪሳራ ያደረሰ ከመሆኑም ባሻገር የሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ እንደነበር ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ በቀድሞ የድርጅቱ አመራሮች የተከሰቱ ሥር የሰደዱ ችግሮችን ለማረምና ድርጅቱን ከዕዳ ለማውጣት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ እንደቆዩና እየተደረጉ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ኢንተርፕራይዙ በአመራር ችግር ምክንያት የገባበትን ዕዳ ለመክፈል እና የኢትዮጵያን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ለመደገፍ ጥንቃቄ የተሞላበት እርምጃ ሲወሰድ መቆየቱንም ነው የተናገሩት።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት የኢትዮጵያን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አቅም ለማሳደግ በመላ ሀገሪቱ በ83 ቅርንጫፎች እየሠራ ይገኛል። ቅርንጫፎቹን ለማስተሳሰር የሚያስችል አዋጭ ስትራቴጂክ ዕቅድ ነድፎ እየሠራ እንደሚገኝ ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ገልጸዋል።

# "አፍሪካ አሁን የሆነችውን ብቻ ሳይሆን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎች እየታዩ እንዲሁም ሥራ ፈጣሪዎች እና የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች እያደጉ በመሆኑ የአፍሪካ የብልጽግና ጉዞ አይቀሬ ነው።

የአፍሪካውያን የፈጠራ ውጤቶች በአህጉሪቷ እንዲሁም ከዚያም አልፈው እየተስፋፉ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አህጉሪቷ እየፈተኗት ያሉ አንዳንድ ችግሮችን ከውስጥ በተፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተከላከለች እንደምትገኝም አስረድተዋል።

አፍሪካ አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት እየተቀላቀለች መሆኑን ጠቅሰው፤ በቅርቡ በኢትዮጵያ አዘጋጅነት የፓን-አፍሪካን ሰው ሠራሽ አስተውሎት ኮንፈረንስ መካሄዱንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ዘላቂ ልማትን ለማስመዝገብ ስልቶችች መቀየሳቸውንም ገልጸዋል።

ምቹ የኢኮኖሚ እድገትን ለማስቀጠል የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማድረግ፣ ምርታማነትን መጨመር፣ ንግድና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ እንዲሁም ኢንዱስትሪን በማስፋፋት ከጥሬ ዕቃ አምራችነት ወደ ከፍተኛ እሴት ወደተጨመረበት ምርት አቅራቢነት መሸጋገር ያስፈልጋል ሲሉ አጽንዖት ሰጥተዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ አፍሪካ ብዙ ታዳሽና አላቂ ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም ኢኮኖሚዋ ግን አዙሪት ውስጥ ገብቶ ቆይቷል፤ በዚህ ምክንያት አህጉሪቷ ለውጭ ጥገኝነት ተጋልጣለች፤ ስለዚህ ዓለም ወደ አንድ መንደርነት ከመለወጧ ጋር በተገናኘ የሚገጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም የሚደረጉ ጥረቶች በፈጠራና እውቀት የታገዙ ሊሆን ይገባል።

በአሁኑ ወቅት የአፍሪካ መሪዎች የልማት መንገዶችን እየቀየሱ መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ድህነትንና መሃይምነትን ከመቀነስ አንጻር ብዙ ውጤቶችን አስመዝግባለች፤ አሁን ደግሞ በምግብ ራሷን ለመቻል ጉዞዋን ጀምራለች ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስን የመቻል ጥረቶችን ሲገልጹ፥ አረንጓዴ አሻራና የበጋ ስንዴ አንስተዋል። አክለውም፣ ሀገሪቷ በቅርቡ የስንዴ ምርትን ወደጎረቤት ሀገራት ለመላክ እንቅስቃሴ ላይ መሆኗንም አብራርተዋል።

ዓለም አፍሪካን የሚመለከትበትን መነጽር እንዲያስተካክል አፍሪካውያን ወጣቶች በትኩረት እንዲሠሩ፤ አፍሪካውያን ስለጎደላቸው ነገር ሳይሆን ስላላቸው ሀብት፣ ውጤታማነትና ተስፋ እንዲያወሩ ጠይቀዋል።

በርካታ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች እየታዩ መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ፈጠራን ጠብቆ ማቆየትና ቴክኖሎጂ ፈጣሪዎችን መደገፍ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ወጣቶች ቢዝነስን መጀመር፣ መምራትና ማስተዳደር እንዲችሉ ለማሰልጠን ኢትዮጵያ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ማእከል መገንባቷን አስታውሰው፤ በቅርቡ የወጣቶቹ ፈጠራና ጥረት ፍሬ ሲያፈራ የነሱን ኑሮ ማሻሻል ብቻም ሳይሆን ለቀጠናው ኢኮኖሚ ትልቅ አስተዋጽዖ እንደሚኖረውም አስረድተዋል።

ለምርታማነት መጨመር፣ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት እውን ለማድረግና ድህነትን ለመቀነስ የክህሎት መዳበር ወሳኝ መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከግማሽ ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች የጎበኙትና የተደነቁበት በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን የሳይንስ ሙዚየም በቅርቡ መመረቁንም አስታውሰዋል።

በመድረኩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አፍሪካውያን ተደራጅተው ለነጻነታቸው እንዲታገሉና ምዕራባውያን ቅኝ ገዢዎችን ከአህጉሪቱ ጠራርገው እንዲያስወጡ ከማድረግና የቀድሞው የአፍሪካ ሕብረት እንዲመሰረት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለስላሴን ጨምሮ 17 የቀድሞ የአፍሪካ መሪዎች በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ቀጣይ ጊዜ ሰላም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አሳስቧል።

አብን ትናንት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው የአማራ ሕዝብ ሰላምና ደሕንነት፣ ዘላቂ ጥቅም እንዲከበርና ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ እየሰራ ነው።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶክተር በለጠ ሞላ እንደገለጹት፤ የትግራይ ሕዝብን ጨምሮ የኢትዮጵያ ቀጣይ ጊዜ ሰላም እንዲሆን ሕወሓት ትጥቅ መፍታት አለበት። የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር አብሮ የኢትዮጵያዊ እምነቱ ተመልሶ ለዘመናት የቆየው ወሳኝ የማህበረ ፖለቲካ ሚናው እንዲመለስ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ሁሉም ባለድርሻ አካላት መንግሥትን በመደገፍ ኢትዮጵያ ሰላም የምትሆንበትን ሁኔታ መፍጠር ታሪካዊ ኃላፊነታችን ነው።

ዶክተር በለጠ በመግለጫቸው፣ የሽብር ቡድኑ ምንም እንኳን መሰረቱ የትግራይ ሕዝብ ቢሆንም፤ በትግራይ ሕዝብ ስም ሲገዛ የቆየ እና ለትግራይ ሕዝብም ያልሆነ ነገር ግን በስሙ ሕዝቡን ለመከራ የዳረገ ነው ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት እስካለ ድረስ ኢትዮጵያ ሰላም ልትሆን እንደማትችል አብን ይገነዘባል ያሉት ዶክተር በለጠ፤ በአንድ አገር ሁለት የታጠቀ አካል ሊኖር ስለማይችል አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ምዕራውያን አገራት ሕወሓትን ለማትረፍ የሚያደርጉትን ሩጫ አብን እንደማይቀበል ገልጸዋል።

ሊቀመንበሩ፤ በአማራና በአፋር ክልሎች የወደሙ መሰረተ ልማቶች መልሶ ለማቋቋም ሰብአዊነት የሚሰማው አካል ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። የተጎዳው ሕዝብ አንገቱን ቀና እንዲያደርግ በጎ አድራጊ ሁሉ ድጋፍ ማድረግ አለበት። በሁለቱም ክልል ሕዝቦች ላይ ከፍተኛ የሆነ ውድመት ደርሷል። ሥነልቦናው የተሰበረ ሕዝብ አንገቱን ቀና እንዲያደርግ የፈረሱና የወደሙ መሰረተ ልማቶችን መልሶ በመገንባት መንግሥትን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የአብን ምክትል ሊቀመንበር አቶ መልካሙ ሹምዬ፤ የአሸባሪው ሕወሓት የተቀበለው የሰላም ድርድር ጊዜ ለመግዛት እንጂ ምንነቱና ስሪቱ ለሰላማዊ ውይይት የሚመች አይደለም። አብን እየተካሄደ ያለውን ድርድር የሚደግፍ ቢሆንም ነገር ግን አሸባሪው ቡድን ካለው ስሪታዊ ባህሪ አንጻር ለሰላም ድርድር ፍላጎት እንደማይኖረው ከቀደመ ተግባሩ መረዳት ቻላል ብለዋል።

ምክትል ሊቀመንበሩ፤ የሽብር ቡድኑ ገና ሲመሰረት ጀምሮ ፋሽስታዊ የሆነ እኩልነትንና ፍትሃዊነትን የሚጠየፍ ቡድን ነው። ቡድኑ ታላቋን ትግራይን ለመመስረት የተነሳ ቢሆንም እድል አግኝቶ በአገዛዝ ዘመኑ የጭቆናና የዘረፋ ሥርዓት ዘርግቶ ቆይቷል። በሕዝብ ትግል ወደመቀሌ ከገባ በኋላም የትግራይን ሕዝብ ሲጠብቅ የነበረውን የአገር መከላከያ ሠራዊትን በማጥቃት ባህሪውን ማሳየቱን ጠቁመዋል።

# ኢትዮጵያ ለስንዴ ግዥ በዓመት የምታወጣውን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ዓመታዊ የስንዴ ፍጆታ በኢኮኖሚስቶችና በዘርፉ ባለሙያዎች መጠናቱን የገለጹት ዶክተር መለስ፤ ከሕዝብ ቁጥሩ ዕድገት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በተሰላው መሰረት የሀገር ውስጥ ዓመታዊ የስንዴ ፍጆታ 97 ሚሊዮን ኩንታል መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር መለስ ከሆነ፤ መሰብሰብ በጀመረው የመኸር ስንዴ ምርት መረጃ መሰረት ደግሞ 108 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል።

አሁን ላይ ከመኸር ግብርና እየተሰበሰበ ያለው የስንዴ ምርት ከአጠቃላይ ፍላጎቱ አንጻር ሲታይ የ 11 ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ እንዳለው ይገመታል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ለስንዴ ግዥ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ከፍላጎት በላይ የሆነውን ምርት ለተለያዩ አገራት ማቅረብ ትችላለች ሲሉ አስረድተዋል።

የመኸር ሰብል በመሰብሰብ ሂደቱ ጊዜና ጉልበትን የሚቆጥብ ከማድረግ ባለፈ የምርት ብክነት ለመቀነስ በሚያስችል ሁኔታ አንድ ሺህ አምስት መቶ ኮምባይነሮች ሥራ ላይ መዋላቸውን ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ ከዚህ ባለፈ በ2015 ዓ.ም በበጋ ስንዴ መስኖ ከአንድ ነጥብ ሶስ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

ከመስኖ ስንዴ ልማቱ 52 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ መገመቱንም ዶክተር መለስ አስታውቀዋል። የስንዴ ልማቱ በዘጠኝ ክልሎች ላይ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጀምሮ በየክለሎቹ አመራሮች የታየው የመስኖ ስንዴን የማልማት ትኩረት ኢትዮጵያን ለውጤት እንዳበቃት ተናግረዋል።

የዓለም የንግድና ፖለቲካ ሁኔታ ችግር በታየበት ወቅት እንዲሁም ኢትዮጵያ ላይ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫናዎች በነበሩበት ወቅት የስንዴ ልማቱ ላይ ትኩረት መደረጉን ዶክተር መለስ አስረድተዋል።

ጫናው በተለያየ መንገድ የመጣ መሆኑን አስረድተው፤ የተለያዩ አካላት ኢትዮጵያ የግብርና ግብዓቶችን በዋናነት የማዳበሪያ አቅርቦት እንዳታገኝ ቢሞክሩም ፈተናው ታልፎ ለአርሶአደሩ ማዳበሪያ መቅረቡን ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ የተለያዩ ጫናዎች በበረቱበት ወቅት የስንዴ ምርትን በአገር ውስጥ ለመሸፈን የተደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው። በቀጣይም የተሻለ ውጤት ለማግኘት ምርት በደረሰባቸው አካባቢዎች በፍጥነት መሰብሰብና በቀጣይም የግብርና ምርታማነት ደረጃን እያሳደጉ መቀጠል ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ከአጠቃላይ የመኸር ምርት 400 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደምታገኝ ይጠበቃል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ 108 ሚሊዮን ኩንታሉ የስንዴ ምርት ነው።

# ከአሸባሪው ትህነግ ነጻ በወጡ የትግራይ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሚደነቅ ነው። ከቀያቸው ተፈናቅለው የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ወደቀያቸው መመለስ መጀመራቸው የሰብአዊ ድጋፍ ለማድረስ የተሻለ መደላድል ይፈጥራል።

አቻ እና ሌሎች የሰብዓዊ ድርጅቶች የሰብዓዊ ድጋፍ ማዕከላት ባሉባቸው ከተሞች ተደራሽነትን ለማሳላጥ በአፋርና በትግራይ ክልል በስፋት እየሰሩ መሆኑንም አንስተዋል፡፡

በመሆኑም መንግሥት የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲዳረስ የጀመረውን ጥረት በመደገፍ አብረን እንሰራለን ነው ያሉት።

ለዚህም የሰብዓዊ ድጋፍ ማስተባበሪያ ቢሮው ከፌዴራል መንግሥትና ከሌሎች በተዋረድ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ድጋፉን ማሳለጥ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ሲመክር መቆየቱን ጠቅሰዋል።

ሚሼል ሳድ አያይዘውም በየክልሉ ያሉ ሰራተኞች ድጋፉን በፍጥነት ለማድረስ ሲጥሩ እንደነበር አስታውሰዋል።

የሰብዓዊ ድጋፍ ድርጅቶች ከሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ስለእንቅስቃሴያቸው መረጃ የሚለዋወጡበት አግባብ መኖር እንዳለበት ገልጸው፤ አቻ በዓመታዊ እቅዱ መሰረት መሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገምና የድጋፍ ፍላጎትን በማጤን ወደ ተግባር ለመግባት እንቅስቃሴ መጀመሩንም ጠቁመዋል።



መንግሥት ከአሸባሪው ሕወሓት ነጻ በወጡ የትግራይ ክልል ከተሞች የሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽ እንዲሆን ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱ ይታወቃል።

አሸባሪው ቡድን ከሕዝብ ጉሮሮ ነጥቆ ለታጣቂዎቹ ለመስጠት ደብቆት የነበረውን የእርዳታ እህል ለሕዝቡ ማከፋፈሉም የሚታወስ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መከላከያ ሠራዊት፡- የሀገር ካስማ፤ የሉዓላዊነት ዘብ!

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከሕዝብ አብራክ የወጣ በመሆኑ ሁልጊዜም ሕዝባዊና ሀገራዊ ተልዕኮዎችን አንግቦ ይንቀሳቀሳል። የሀገሪቱን ሉዓላዊነትን ለማስከበርና የዜጎችን ሰላም ለማረጋገጥ መስዋዕትነትን ይከፍላል። በዱር በገደሉ ይዋደቃል። ደሙን ያፈሳል፤ አጥንቱን ይከሰክሳል።

የመከላከያ ሠራዊቱ አልፋና ኦሜጋ የሀገር ሉዓላዊነትና የሕዝብ ደህንነት ናቸው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በጀግንነቱ ሁሉም በአንድ ድምጽ የሚስማማበት በሰላም ጊዜ የልማት አርበኛ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር ጀግና ሠራዊት ነው። ሠራዊቱ እንደ ንብ በኅብረት የሚያጠቃ እንደ አንበሳ ሉዓላዊነትን የማያስደፍር ጀግና መሆኑንም ብዙዎች ይስማሙበታል። ሠራዊቱ ድል የሚፈጥር፣ ሞትን የሚያሸንፍ፣ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር፣ ፍላጎቱን ለዓላማው የሚያስገዛ፣ የነፃነትን ዋጋ ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ጨለማን ማሻገር የሚችል ልበ ሙሉ ነው።

የዚሁ ሠራዊት አንድ አካል የሆነውም የሰሜን ዕዝ የሀገርን ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን ለማስከበርና የሕዝቦችንም በሰላም የመኖር ዋስትና ለማረጋገጥ መስዋዕት የከፈለ ጀግና ሠራዊት ነው። የሰሜን ዕዝ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተካሄደውን ጦርነትን ተከትሎ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ጀምሮ በትግራይ ክልል ውስጥ ሰፍሮ የነበረ ሲሆን አገሪቱ ካላት ሠራዊት ውስጥ በሰው ኃይልና በታጠቀው መሳሪያ አንጻር ግዙፉ እንደነበረ ይታመናል።

የሰሜን ዕዝ ለሃያ ዓመታት በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ እየተኛ የትግራይ ሕዝብን ጠብቋል። ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ ማውጣት ከ 1 ሺህ ኪሎ ሜር በላይ መንገድ ሰርቷል፤ 65 ትምህርት ቤቶችን ገንብቷል፤ ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ በማዋጣት የወጣቶች መዝናኛ ገንብቷል፤ ከ23ሺ ሄክታር በላይ ማሳ በማረምና ሰብል በመሰብሰብ አጋርነቱን አረጋግጧል። ሆኖም ለዚህ ጀግና ሠራዊት የጠበቀው ሽልማትና ማበረታቻ ሳይሆን ገፍና በደል ነው።

የአሸባሪው የሕወሓት አመራሮች ጥቅምት 24 ቀን 2013 የሰሜን ዕዝን ከጀርባው በመውጋት ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍ ፈጽመዋል። ለዘመናት የትግራይ ሕዝብ ዋስትና ሆኖ የቆየውን ኃይል በማጥቃት ኢትዮጵያን የማፈራረስ ተልዕኳቸውን አሃዱ ብለው ጀምረዋል። አሸባሪ ቡድኑ በአገሪቱ ትልቁ እንደሆነ በተነገረው የሰሜን እዝ ላይ ያደረሰው ጥቃት በሚገባ ታስቦበትና ታቅዶ የዕዙን ጦር መሳሪያዎች ለመቆጣጠር ያለመ ነበር። የሽብር ቡድኑ ሰሜን ዕዝን በመደምሰስ ከቻለ ሥልጣን መልሶ መቆጣጠር ካልቻለም የተዳከመች ኢትዮጵያን በመፍጠር ሀገሪቱን ለባዕዳን ኃይል አሳልፎ የመስጠት ተልዕኮ ይዞ ተንቀሳቅሷል።

ሆኖም ጀግናው መከላከያ ሠራዊት ከሕዝብ ጋ በመጣመር አሸባሪ ቡድኑን አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት ህልሙን አክሽፎታል። ከአንድም ሶስት ጊዜ የከፈታቸውን ጦርነቶች በመመከት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስከበር ችሏል። የመከላከያ ሠራዊት በአሸባሪ ቡድኑ በተደጋጋሚ የሚቃጡ የህልውና አደጋዎችንም በማምከን አኩሪ ተግባር በመፈጸም ላይ ይገኛል።

ሠራዊታችን ባለፉት ሁለት ዓመታት ከሽብር ቡድኑ ጋር አያሌ ውጊያዎችን ሲያደርግ ብዙ ዋጋ ከፍሏል። በየጦር ውሎው በጀግንነት እየተዋጋ ለእናት ሀገሩ ተሠውቷል። ለሀገርና ለወገን ያለውን አጋርነት በንግግር ሳይሆን በተግባር አሳይቷል። አሁንም ሀገርን ለመከላከል በዱር በገደሉ እየተዋደቀ ነው። በዚህም መከላከያ ሠራዊት በከፈለው መስዋዕትነት የትግራይ ሕዝብ ከባርነት ነጻ ሊወጣ ጫፍ ላይ ደርሷል።

ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት እየከፈለ ባለው መስዋዕትነት ሃምሳ ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ በአሸባሪው ትህነግ ቀንበር ውስጥ ሲማቅቅ የቆየው የትግራይ ሕዝብ የነጻነት ብርሃን ሊያይ ጥቂት ጊዜያት ብቻ ቀርተውታል። የመከላከያ ሠራዊቱ መሥዋዕትነት የታሰበውን ግብ እንዲያሳካ የትግራይ ሕዝብ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። የመከላከያ ሠራዊቱን በመንከባከብ፣ ስንቅ በማቀበል፣ ስለተደበቁ ጀሌዎችና የጦር መሣሪያዎች መረጃ በመስጠት፣ መንገድ በመምራት እና አካባቢውን በመጠበቅ የትግራይ ሕዝብ ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፏል። በዚህም የሽብር ቡድኑ ጀንበር ወደ መጥለቋ ተቃርባለች።

በመሆኑም በነገው ዕለት «መቼም አንረሳውም» በሚል መሪ ቃል የሚከበረውን ሁለተኛውን የሰሜን ዕዝ ጥቃት መታሰቢያን ስናከበር የመከላከያ ሠራዊት የከፈለውን መስዕዋትነት እውቅናና ክብር በመስጠት እና ጥቃቱ ሀገርን የማፍረስ ዕቅድ አካል መሆኑን በማስታወስ ሊሆን ይገባል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# እንክርዳዱ መልሶ እንዳይበቅል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

መልካም ነገር በመዝራት ያማረ ፍሬ እንደሚገኝ ሁሉ፤ መጥፎ ዘር መዝራትም ከግለሰብ እስከ በማህበረሰብ ብሎም በአገር ላይ የሚያደርሰው ኪሳራ የትየለሌ ነው። ዘር መዝራት ስንል ታዲያ በጥሬ ቃሉ ትርጉም የምናገኘው የግብርና ሥራን አልያም ተክል መትከል ሳይሆን በሕይወት ዘመናችን የምናደርገው ማንኛውንም እንቅስቃሴ ይመለከታል።

በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን መንገዳችን ቀና ከሆነ ያማረ ፍሬን እናፈራለን፤ በተቃራኒው ደግሞ መንገዳችን ያልተገባና ጤናማ ካልሆነ ውጤቱ ረብ የለሽ ይሆንና በዘራነው መጥፎ ዘር ትውልዱ መከራ እንዲያጭድ ምክንያት እንሆናለን። እኛም በዘራነው የጥፋት ዘር ዋጋ መክፈላችን የማይቀር ነው።

ዛሬም በአገራችን እየሆነ ያለው ይሄው ነው። የአሸባሪው ትህነግ አመራሮች የስልጣን ጥማት እና የከፋ እራስ ወዳድ የተነሳ አገርና ህዝብ በብዙ መከራ እየተፈተነ ይገኛል። እየከፈለ ያለውም ዋጋም የትየለሌ ሆኗል።

ቡድኑ ባለፉት 27 ዓመታት በምድሪቷ የዘራው ክፉ የዘረኝነት ዘር መከራ ሆኖ እየታጨደ ነው። ከመከራም በላይ የጋንግሪን ቁስል ሆኖ እየገዘገዘን ነው። ይህ መርዝ ታዲያ መልሶ እንዳይበቅል ከስሩ መንቀል ለነገ የምናሳድረው የቤት ስራችን አይደለም።

ቡድኑ ‹‹ጦርነት የገበጣ ጨዋታችን ነው›› በማለት በእብሪትና በማን አለብኝነት የለኮሰው እሳት እሞትለታለሁ እያለ ከሚያስጨርሰው የትግራይ ህዝብ ባለፈ በመላው አገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ምስቅልቅሎሽን ፈጥሯል።

ነገ ሁለተኛ አመቱን በሚያስቆጥረው የሰሜኑ ጦርነት በአሸባሪው ትህነግ እብሪት ተለኩሶ ዛሬም ድረስ እሳቱ አገርና ህዝብን እየለበለበ ይገኛል። ቡድኑ በለኮሰው በዚህ እሳት የትግራይ፣ የአማራና የአፋር ሕዝብ አላስፈላጊ ዋጋ ለመክፈል ተገዷል።

እየተከፈለ ባለውም ዋጋ መላው ኢትዮጵያዊ ውስጡ ቆስሏል፤ ታሟል። ህዝቡ ከዚህ ህመሟ ማገገም እንዲቻል መንግሥት የሰላም አማራጮችን በተደጋጋሚ ሲያቀርብ እንደነበር ይታወሳል። ይሁንና መንግሥት በተደጋጋሚ ያቀረበውን የሰላም አማራጭ ወደ ጎን በመግፋት ለሶስተኛ ጊዜ የተጀመረው ጦርነት በምንም መንገድ ቢሆን መቋጫ ሊበጅለት እንደሚገባው በብዙዎች ዘንድ ይታመናል።

መቋጫው እየተናፈቀ ያለው ይኸው የሰሜኑ ጦርነት በጊዜ ሊቋጭ ያልቻለው ቡድኑ የትግራይን ህዝቡ መያዣ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ስለመሆኑ ለመናገር የሚከብድ አይደለም። ቡድኑ ይህንኑ እውነታ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በተለያየ መንገድ ሲገልጽ መስማት የተለመደ ነው።

ይህንንም አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጦርነቱ በተጀመረበት በ2013 ዓ.ም መገባደጃ ላይ አገር እያፈረሱ ያሉትን ጥቂት ግለሰቦች ከትግራይ ሕዝብ ነጥሎ ለማውጣት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት እንደሆነ ገልጸዋል። በወቅቱም “አረሙ እንዲነቀል አድርገን እንሠራለን። አረሙን ስንነቅል ግን ስንዴውን እንዳንጎዳው የሚቻለውን ሁሉ ጥንቃቄ እናደርጋለን” በማለት ነበር መልዕክታቸውን ያስተላለፉት።

ከዚህ አሸባሪ ቡድን ጋር እየተደረገ ያለው ጦርነት ብልሃት፣ ጥንቃቄና ጊዜ የሚፈልግ ነው። እርግጥ ነው ቡድኑ አገር ከማተራመስ እስከ ማፍረስ የሚዘልቅ አጀንዳውን ለማስቀጠል የትግራይ ህዝብን መያዣ አድርጎ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል። ይህ ደግሞ ጦርነቱን ፈታኝና ውስብስብ ማድረጉ አይቀሪ ነው።

ያም ቢሆን ታዲያ አረም ያው አረም ነውና የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር መነቀሉ የግድ ነው። ሲነቀልም መልሶ እንዳይበቅል ከስሩ መንቀል ሁነኛ መፍትሔ ከመሆኑም በላይ ‹‹ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል›› የሚለው ተረት እንዳይደረስ በማያዳግም መልኩ ምንጩን ማድረቅ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያን የገጠማት ጠላት የውጭ ወራሪ ሳይሆን የስልጣን ጥማት ያናወዘውና የገዛ አገሩን ለማፍረስ የተዘጋጀ ነቀርሳ ባንዳ ነው። ይህን የአገርና የህዝብ ነቀርሳ የሆነን ቡድን መልሶ እንዳይበቅል አድርጎ የመንቀሉ እውነታ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የሚቀር አይደለም ።

‹‹ለሁሉም ጊዜ አለው›› እንዲል ታላቁ መጽሐፍ ዛሬ የትግራይ ህዝብን መያዣ አድርጎ እየነገደ ያለው ይህ ቡድን ጉም ሆኖ የሚተንበት ጊዜ ሩቅ አይመስልም። ለዚህም ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ለአንዲት ኢትዮጵያ መቆማቸው ብቻ በቂ ነው።

ቡድኑ የትግራይን ህዝቡ መያዣ አድርጎ የጀመረውን ጦርነት ለዘለቄታው በማስቆም ወደ ጀመርነው የልማትና የብልጽግና ጎዳና በሙሉ አቅማችን ለመመለስ ህዝብ በአንድ ልብ ከመንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል። ኢትዮጵያን እየተፈተነች ያለችው በምታውቃቸው የውስጥ ባንዳዎች ብቻ ሳይሆን በብዙ አደባባይ በሙሉ ጠላቶች ነው። ለዚህ ደግሞ በአንድነት መቆም የግድ ነው።

ጦርነቱ የቱንም ያህል እልህ አስጨራሽ ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት እህሉን ከገለባ የመለየት ሥራ ጊዜ ወስዷል። በአውደ ግንባር ያለው እውነታም የጦርነቱን የመቋጫ ጊዜ የሚያሳብቅ ከሆነም ውሎ አድሯል፤ ለዚህም ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን የአላማ ጽናት እና ሕዝባዊነት ከፍ ብሎ የሚታይ ነው።

ሠራዊቱ ድንጋይ ተንተርሶ፣ ጤዛ ልሶና ደረቱን ለጥይት ሰጥቶ እየከፈለ ባለው መስዋእትነት አገርና ህዝብን አንገት ከመድፋት አውጥቷል፤ የጠላቶቻችንም ሟርቱ ከንቱ እንዲሆን አድርጓል። ለዚህም ከፍ ያለ ክብር ይገባዋል።

በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን ግዞት ውስጥ ወድቆ ረሃብ የጠናበት የትግራይ ህዝብም ዛሬ ነጻ እየወጣ መሆኑ ዕለታዊ ዜና መሆን የቻለው በጀግኖች ኢትዮጵያውያን ደም ነውና ዳግም ክብር ይገባቸዋል።

ከድል ዜናው ባሻገርም የትግራይ ህዝብ በቡድኑ ከገባበት የሰቆቃ ሕይወት ነጻ እንዲወጣ መንግስትና መላው ህዝብ በርካታ የቤት ሥራዎች አሉባቸው። ቡድኑ በአገሪቷ ካደረሰው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ በበለጠ በትግራይ ህዝብ ላይ ያደረሰውን የስነ ልቦና ስብራት በቶሎ ማገገም እንዲችል የኢትዮጵያውያን ርብርብና ትብብር ለነገ የሚባል አይደለም።

በጦርነቱ የመጨረሻው ምእራፍ የምዕራቡ ዓለም በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ እየበረታ የመምጣቱ አውነታ፤ ለቡድኑ ሕይወት ለመስጠት የሚደረግ ዓለም አቀፍ ዘመቻ መሆኑን በመገንዘብ አንድነታችንን በማጠናከር ዘመቻውን ለመቀልበስ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

# ተጠየቅ

# ‹‹ከታህሳስ ጀምሮ በኤሌክትሮኒክስ ስርዓት ያልተመዘገበ አቅራቢ በማንኛውም ጨረታ ላይ መሳተፍ አይችልም››

**አቶ ሐጂ ኢብሳ**
**የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን፤ በአገር ደረጃ የግዥ ሥርዓትን መዘርጋት፣ የተዘረጋው ሥርዓት መሥራት አለመሥራቱን ማረጋገጥና ጥናት ማድረግ ብሎም ለውጦች ካሉ ማሻሻል እና በአዋጅና መመሪያ መሠረት መተግበሩን ይከታተላል። በግዥ ላይ መንግስትን የማማከር፣ በአገር ደረጃ ግዢን የተመለከቱ ስልጠናዎችን መስጠት፣ ማንዋል ግዥን ወደ ኤሌክትሮኒክስ የመለወጥ፣ ንብረትን የመቆጣጠር፣ ግዥ ላይ በሚሰጡ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ጥቆማዎች መሰረት ኦዲት የማድረግ ሥራን ይሠራል። ግዥና ጨረታ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በአቤቱታ ሰሚ ዳይሬክተር በኩል መስማትና ልክ እንደ ከፊል ፍርድ ቤት የቦርድ የዳኝነት ሥርዓት መስጠትም የባለስልጣኑ ዋነኛ ተግባር ነው። እነዚህን መሠረት በማድረግ ተቋሙንና አሰራሩን የተመለከቱ ጥያቄዎችን ይዘን ከባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል የተቋማት ግዥዎች በተለያዩ መንገዶች ይፈጸሙም እንደነበር ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት የሚተገበረው ከፌዴራል እስከ ክልል የተሰናሰለው የግዥ ሥርዓት በመጀመሩ ምን ማትረፍ ተችሏል?**

**አቶ ሐጂ፡-** ለረጅም ዓመታት ግዥ የሚፈጸመው በገንዘብ ሚኒስቴር ስር ባለ አንድ ዳይሬክተር ነበር። በዚህን ጊዜ እያንዳንዱ ተቋም የየራሱ ህግ ነበረው። በኋላ ሲታይ የዓለም ግዥ አካሄድ በዚህ መልኩ ስላልሆነ በዚያው በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ከዳይሬክተር ከፍያለ ዩኒት ይዞ ተቋቋመ። በኋላ የዓለም ባንክም ሆነ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ በዓለም የሌለ አካሄድ ነው በማለታቸው፤ ራሱን ችሎ እንዲወጣና ከተጽዕኖ ነፃ ሆኖ እንዲሠራ የሚል አቅጣጫ ተቀመጠ። ይህ ብቻ አይደለም በርካቶቹ በውጭ ጫና ውስጥ ነበሩ። ለምሳሌ ቀደም ሲል ገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ዳይሬክተር ተብሎ በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ነበር። ነገር ግን የዓለም ባንክም ሆነ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ በዓለም የሌለ ተሞክሮ ነው ብለው፤ በሒደት ወደ ሚኒስቴር ደረጃ አደገ።


ብዙዎቹ ወደዚህ የደረሱት የዓለምን ተሞክሮ ወስደው ነው። ስለዚህ ይህ ተቋምም 1997 ዓ.ም የግዥ ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተብሎ ተመሰረተ። የሚኒስትሮች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263 መሰረት ደግሞ ባለስልጣን ሆነ። በዚህም የተጨመሩለት ኃላፊነቶችና ሥልጣኖች አሉ።

ባለስልጣን ሲባል አደረጃጀቱ ሙሉ ለሙሉ የተለወጠበት ሁኔታ አለ። በፊት ከነበረው ኃላፊነት በተጨማሪ የምርምር ሥራዎችን እንዲሰራ የታሰበ ሲሆን፤ ተጠያቂነትና ሚዛናዊነት እንዲኖር ተደርጎ የተቋቋመ ነው። ገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ በዳይሬክተር እያለ ተጠሪነቱ ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ስለሆነ በዚያው ይቀራል። አሁንም ተጠሪነቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ነው። አሁን ግን በነፃነት ብዙ እርምጃ መሄድ ይችላል፤ የጥቅም ግጭት የሚፈጠር ከሆነ ባለስልጣኑ በራሱ የሚወስናቸው ጉዳዮች ይኖራሉ፤ ተጠሪ ስለሆነ ብቻ ህጉ የማይለውን ነገር አይሠራም።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ከኤጀንሲ ወደ ባለስልጣን ከተሸጋገረ በኋላ ተልዕኮውን እንዴት እየተወጣ ነው?**

**አቶ ሐጂ፡-** ከባድ ነው። እዚህ አገር ላይ ሌብነት አለ ከተባለ አንዱ በየከተማው መሬት አካባቢ ያለው ሌብነት ነው። ሁለተኛው ገቢዎች አካባቢ ከታክስ አሰባሰብ ጋር ያለው ሲሆን፤ ሦስተኛው ግዥ ነው። ግዥ ሙሉ ለሙሉ ችግር አለበት ብሎ መውሰድ ይቻላል። እኛ እንደ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ብንቋቋምም 169 የፌደራል ተቋማት አሉ። ከትልቅ እስከ ትንሽ ያለውን ግዥ ሁሉ አንቆጣጠርም።

በዋናነት እየሠራን ያለነው ማሰልጠን፣ ማብቃት፣ ኦዲት ማድረግ፤ ጨረታዎች ላይ ክርክር ሲመጣ ክርክሩን ማየት፤ ወጥቶ መገምገም ነው። ከየቦታው ጥቆማዎች ይመጣሉ፤ ጥቆማዎቹንም ያያል። ተልዕኮውን መቶ በመቶ አሳክቷል የሚል እምነት የለኝም። ምክንያቱም ሌብነት ባልቆመበት ሙሉ ለሙሉ አሳክተናል ማለት አንችልም። ነገር ግን



ባለስልጣኑ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል።

ለምሳሌ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ላይ ጥቆማ ደረሰን። ሙሉ ለሙሉ የአገሪቱን ግዥ ሥርዓት ወደ ጎን በመተው የሚሰራበት ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር። ከገንዘብ እና ትምህርት ሚኒስቴር ጋር ተነጋግረን ሄደን ኦዲት አድርገን ከፍተኛ ችግር አገኘንበት። መልሰን ሙሉ ኦዲት ሲደረግ ብዙ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ጉዳዮች መኖራቸውን ተረዳን። አንድም ግዥ ሥርዓት ተከትሎ የተሠራ ሥራ አልነበረም። አንድ ህንፃ ማሰራት ቢያስፈልግ አንዱን ጠርቶ ማሰራት ነበር፤ ውል የለም፣ ተጠያቂነት የሚባል ነገርም የለም። በዚህ የተነሳ በርካታ ሰዎች ከኃላፊነታቸው ተነስተዋል።

መዝገብ እየተጣራ ለመርማሪ ፖሊስም አስፈላጊ ሰነዶች ተሰጥተዋል። ሰነዶቹ ተጣርተው ማለቅ አለባቸው። አንዳንዶቹ የፓርላማ አባልም ስለሆኑ ያለመከሰስ መብታቸው ተነስቶ ለህግ ማቅረብ የግድ ይሆናል። ከዚህ ውጭ ሌሎች በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችም አጠቃላይ በጀታቸውን እስከተወሰነ ድረስ እስከማስያዝ ደርሰናል።

አርሲ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ግዥ በጠቅላላ በትውውቅ ነበር። ያጠፉትን ማስተካከል አለባቸው ብለን አጠቃላይ በጀታቸውን ይዘናል። ወደ ሥርዓት መግባት አለባቸው። በጀት የህዝብ ነው። ደመወዝ የሚከፍለው እኮ ህዝብ ነው። መንግስት የምንለው ከህዝብ ሰብስቦ፤ መልሶ ለህዝብ የሚሰጥ ነው። በዚህ ደረጃ ብልሹ አሰራር ካለ ሙሉ ለሙሉ በጀት ማቆም ይቻላል። ከዚያም የሚመለከተው አካል ይጠራል፣ ይገመገማል፣ ይነገረዋል። ስህተቱን ካረመ በኋላ በጀቱ ይለቀቃል። በዚህ ልክ እየያዝን ደጋግመን ኦዲት አድርገን አንቀብልም ያሉን አካላት ደመወዛቸው ሲያዝ እስከ ትልልቅ ኃላፊዎች ድረስ ጨኸት ነበር። በኋላ ግን እስከ ፕሬዚዳንት ድረስ መሳሳታቸውን አምነውና ተፀፅተው ወደ ህግ የሚሄደውን ወደ ህግ በመውሰድ በጀቱ እንዲቀጥል አድርገናል።

ስልጠናም እየሰጠን ነው። ዋናው ችግሩ ዩኒቨርሲቲው የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚሳተፉበት ነው። ጨረታ ቢወጣም እንዴት እንደሚከላከሉት አይታወቅም፤ ግን የሚያሸንፉት የተለመዱት ናቸው። አሁን ያንን የተበላሸ አሰራር አስተካክለዋል።

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲም በተመሳሳይ የተበላሸ አሰራር ነበረበት። የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንት ፈላጭ ቆራጭ ነበር። ኮንስትራክሽን ዋጋ ላይ እራሱ ይወስናል። እንጀራ ግዢ ላይ የፈለገውን ዋጋ ይጨምራል። ግን ጭማሪ የራሱ ቀመር አለው። ማን ቀመሩን እንደሚወስን አሰራር አለ። አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የነበረው ግዥ፣ ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና፣ ኦዲተር ከሥራ ውጪ ነበር። ፕሬዚዳንቱም አይሰራም፤ ምክትል ፕሬዚዳንቱ በሁሉም ፈላጭ ቆራጭ ነበር። ሰውየው አሁን በህግ አግባብ እየተጠየቀ ነው።

ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ እንጨት ግዥ ላይ ያጋጠመን፤ እዚያው ፋይናንስ ግዥ የነበሩ አካላት ነጋዴዎች ናቸው። ስለዚህ በየቀኑ ክስ ነበር። በጣም የተበላሸ አሰራር ነበር። እዚያም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጥተን፣ ጥፋቱን የሚሰሩ ግለሰቦች ከኃላፊነት ተነስተው ተጠያቂ እንዲሆኑ አድርገናል። ለምሳሌ ጨረታ አውጥተው ያሸነፈው አካል እያለ ያላለፈውን ይመርጣሉ። በዚህ ብቻ እስከ 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር መንግስት እንዲያጣ አድርገዋል። ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ እና ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ላይ የጎላ ባይሆንም እንዲስተካከል ተደርጓል።

የዩኒቨርሲቲዎች ነገር በጣም ውስብስብ ነው። ስለዚህ ስለተቋሙ ቀድመው ተንብየው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በወቅቱ ተገቢውን ሥራ ሳይሰሩ ቆይተው ለግዥ ድንገት ልዩ ፈቃድ ይጠይቃሉ። ልዩ ፈቃድ ደግሞ በግዥ ትርጉም አለው። ይህ ማለት ግዥው ለሆነ አካል እንዲሰጥ ፈልገዋል ማለት ነው። ይህ ካልሆነ በህጋዊ መንገድ መሥራት ይችላሉ።

ግዥ ማለት አስቸጋሪ ባህሪ ያለው ነው። ኃላፊው ከእቅድ ይነሳል። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት 169 ከሚሆኑ የፌደራል ተቋማት ውስጥ 60 የሚሆኑት የፌደራል ተቋማት የግዥ እቅድ አላቀረቡም። አሁን የበጀት ዓመቱን ሩብ ዓመት አጠናቀናል። ህጉ የሚለው ደግሞ ቀድማችሁ እስከ ሃምሌ 30 አሳውቁ ነው። ፓርላማ የአገሪቱን በጀት ካፀደቀ በኋላ ተቋማት እቅዳቸውን ከልሰው ይልካሉ። ልክ ይህ በጀት እንደተፈቀደ ተቋማት የግዥ እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው። ግን ብዙ ተቋማት ብድግ ብለው የግዥ እቅድ ያቀርባሉ።

ዓመቱን ሙሉ ቁጭ ብለው በመጨረሻ አካባቢ ከፍተኛ ግዥ የሚያቀርብበት ምክንያትም አንዱ በዚህ የተነሳ ነው። በዚህ ወቅት ደግሞ ወደ ጨረታ አይሄድም፤ ወደ ልዩ የግዥ ፈቃድና ውስን ጨረታ፣ ለአንዱ ቀጥታ መስጠት ወደሚለው ይሄዳል። አልፎ አልፎ የተወሰኑ ተቋማት ደግሞ እቅዳቸው እና ሥራቸው ተናቦ የሚሄዱ አሉ። በርካታ ተቋማት ግዥ የሚያካሂዱት፣ ስልጠና የሚሰጡት በዓመቱ መጨረሻ ነው። ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው?

በአሁኑ ወቅት ስልጠና እየሰጠን ነው። 169 የፌደራል ተቋማት ስልጠና ሰጥተን አጠናቀናል። የግዥ ጉዳይ የሚመለከታቸውና ለምሳሌ ፋይናንስና ግዥ፣ የውስጥ ኦዲትና ለመሳሰሉት ከ5000 ያላነሱ ሰዎች ስልጠና ሰጥተናል። ስልጠናውን የምንሰጠው በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሲሆን፤ እውቀቱን ይዞ ዓመቱን ሙሉ እንዲሠሩ ነው። አንዳንዶች ስልጠና የሚሰጡት ዓመቱን ሙሉ ቁጭ ብለው ግንቦት ላይ ነው። ይህ ዓላማ ቢስ፣ የባከነ፣ የሌብነትና ገንዘብ እንዳይተረፍ የሚሰጥ ስልጠና ነው። ማሰልጠን ካለብንና መጠናቀቅ ያለባቸው በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ወቅት መሆን አለበት።

እኛ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ስልጠና እንሰጣለን። በሁለተኛው ሩብ ዓመት የሰጠነው ስልጠና ውጤት ማምጣት መቻሉን ወጥተን ግምገማ እናደርጋለን። ሙስና መቀነስ አለመቀነሱን፣ የግዥ እቅድ መኖር አለመኖሩን እናያለን። የግዥ እቅድ የሌለው አካል አይስተናገድም። የገንዘብ ሚኒስቴር በጀታቸውን ሊለቅ ይችላል። አሁን ግን ደብዳቤ አዘጋጅተን እያሰራጨን ነው። ለፓርላማ፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር የግዥ እቅድ የሌላቸው ስለሆነ በጀታቸውን ያለአግባብ የሚጠቀሙ ተቋማት ብለን እናሳውቃለን። 60 የፌደራል ተቋማት የግዥ እቅድ የላቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- በእርስዎ አባባል 60 የፌደራል ተቋማት የግዥ እቅድ የላቸውም። ታዲያ ግዥ እንዴት ይፈጽማሉ?**

**አቶ ሐጂ፡-** እንግዲህ ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር መንግስት ለእያንዳንዱ ኃላፊ ሰጥቷል። አንድ ብቸኛ ተቋም ይህን ሁሉ ተቋም እየኮረኮመ ማስተካከል አይችልም። በተለይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ የሚመሩት በሚኒስትር ነው። ግንባር ቀደም መሆን አለባቸው የእኛ አለቆች ናቸው። ሚኒስቴር ሆኖ የግዥ እቅድ ከሌለው ሚኒስቴር ነኝ ማለትም አይችልም። ለምን ከተባለ የዚህ አገር 70 ከመቶ በጀት የሚውለው ለግዥ ነው። ከ761 ቢሊዮን ብር የአገሪቱ በጀት ውስጥ 560 ቢሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ ለግዥ ይውላል። ይህ የውስጥ ገቢን ሳይጨምር ነው። አንዳንድ ተቋማትም ከውጭ ብድርና እርዳታ የሚያገኙ አሉ፤ ይህን ሳይጨምር ነው።

የእኔም ተቋም ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ 70 በመቶ በሚሆነው በጀት ካልታቀደ ተቋም አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ይወስደናል። በዚህ ልክ ከፍተኛ ክፍተት አለ። ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ ለሙሉ እቅዳቸውን አቅርበዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ሚኒስቴር ሆኖ የግዥ እቅድ ያላቀረበ አለ?**

**አቶ ሐጂ፡-** ሚኒስቴር ጨምሮ 60 የሚሆኑ የፌደራል ተቋማት እቅዳቸውን አላቀረቡም። ስማቸውን መዘርዘር አልፈልግም፤ ምክንያቱም ወደ ፓርላማ እና ገንዘብ ሚኒስቴር ሄዶ እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ዝርዝሩን መውሰድ ይቻላል። እነዚህ 60 ተቋማት እቅድ አልባ ቢሆኑም ግዥ ይፈጽማሉ። ዛሬ እኮ ግለሰብ እንኳን ያቅዳል። አንድን የመንግስትን ተቋም የሚመራ ኃላፊ ግን እቅድ የለውም ማለት ምን ማለት ነው? የጠፍ ብር አይደለም፤ በዚህ ልክ ችግሮች አሉ። እንግዲህ ሁሌ ሥራ አለ፤ ችግር አለ፤ ግን ተጠናክሮ ተልዕኳችን ለማሳካት መሥራት ጠቃሚ ነው።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ



**የግዥ እቅድ ሳይኖር ግዥ መፈፀም ደረቅ ወንጀል ነው። ማንኛውም ተቋም ያለ እቅድ ግዥ ቢፈጽም ህገ-ወጥ ነው። አጥብቀን እንከታተላለን፤ ለፓርላማም እናሳውቃለን። ገንዘብ ሚኒስቴርም በጀት መከልከል እንደሚችል እናሳያለን**

**አዲስ ዘመን፡- በመንግስት ግዥ ላይ ከሚነሱ ችግሮች አንዱም የጥራት መጓደልና በወቅቱ አለማቅረብ ነው። የችግሩ ምንጭ ምንድን ነው?**

**አቶ ሐጂ፡-** በመንግስት ግዥ ላይ የጥራት ችግር የሚነሳው በዋናነት የሚመለከተው የግዥ አገልግሎትን ነው። በግዥ አገልግሎት ላይ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ችግር አለ። አንደኛው የችግር መነሻ እና መድረሻ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ያለው ገበያ የተረጋጋ አለመሆን ነው።

‹‹ኮመን ዩዘር አይተም›› ሲገዛ ውል የሚገባው ለዓመትና ለሁለት ዓመት ነው። ውል በሁለት ቦታ ይገባል። አንደኛው፤ የግዥ አገልግሎት ጥቅል ውል ይገባል። ዝርዝር ውል ደግሞ እያንዳንዱ ተቋም ይገባል። አቅራቢው ጥቅል ውል ከገባ በኋላ የገበያው ሁኔታ በጣም ይቀያየራል። በዚህ የተነሳ የንግድ ማህበረሰብ ፊት ለፊት መጥተው ቅጣት እንቀበላለን እንጂ ማቅረብ አንችልም ይላሉ። ለምሳሌ ነዳጅ በሊትር ከ30 ብር በአንድ ጊዜ ወደ 60 ብር ዋጋው አድጓል። ሁላችንም ለነዳጅ በጀት ይዘናል። አሁን ግን ዋጋው በእጥፍ ሲጨምር፤ ከሌላ በጀት ወደዚህ ማምጣት ሊጠበቅብን ነው። የኮንስትራክሽን ዘርፍም በዚህ ሁኔታ ትልቅ ፈተና ያለበት ነው። ግብዓቶች በጣም እየጨመሩ ነው። በዚህ የተነሳ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ሥራዎች የሚቆሙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

ሌላው በመንግስት ግዥ መጀመሪያ ናሙና ይመጣል፤ ከዚያ ይታያል። ክፍያ የሚፈፀመው በውሉ መሰረት ሲቀርብ ነው። ነገር ግን ጅቡቲ ወደብ ላይ ገዥ ካገኙ ወዲያውኑ አየር በአየር ይሸጣሉ። በዚህ የተነሳ ወደአለማቅረብ የሚሄዱ አሉ። ተሳክቶ እንኳን ቢመጣ ሌብነቶች አሉ። ለምሳሌ የደንብ ልብስ ብቻ ብንወስድ፤ በናሙና የሚወሰደውና የሚቀርበው በቀለም የሚመሳሰል ይሆንና በጥራት ከናሙናው ጋር የማይጣጣም ይመጣል። ወረቀት 100ሺ ደስታ የሚገዛ ቢሆን፤ እያንዳንዱን ነጥሎ ማየት አይቻልም። በዚህም ከጥራት በታች የሆነ ይቀላቀላል። አንደኛ ደረጃ ተብሎ ሦስተኛ ደረጃ ይቀርባል። በአጠቃላይ በዚህ ዙሪያ የጥራት እና በወቅቱ አለማቅረብ ችግር አለ።

አንዳንድ ተቋማት ደግሞ ወዲያውኑ የሚፈልጉ ናቸው። ለምሳሌ ቀለም እና ወረቀት የሚጠቀም ተቋም አቅራቢው እስኪያቀርብ ሥራውን ማቆም ስለሌለበት በግዴታ ወደ ልዩ ፈቃድ ይመጣል። በራሳችን እንግዛ የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች ቀርበውልናል። ለምሳሌ ለዩኒቨርሲቲዎች ክፍት አድርገናል። የትምህርት ጥራትን ለድርድር አናቀርብም። ከትምህርት ጥራት ጋር በቀጥታ የሚገናኙትን ራሳቸው እንዲገዙ ለቀናል። የትምህርት ጥራት ከወደቀ አገር ይወድቃል። የዓለም ገበያ መዋዠቅ በተለይም በራሺያና ዩክሬን ጦርነት የተነሳና፣ በአቅራቢዎች በወቅቱ አለማቅረብና የጥራት መጓደል ችግሮች አጋጥመውናል።

ተቋማት ራሳችን ለምን አንገዛም? የሚል ጥያቄ አላቸው። እኛ ደግሞ በወቅቱ አለማቅረባችን ሌላው ችግር ነው። ይህን ለማቃለል ያደረግነው ጥረት ቢኖር ባለፉት ሁለት ዓመታት፤ በመጀመሪውና ሁለተኛው ሩብ ዓመት የተመደበው አቅራቢ ማቅረብ ካልቻለ፤ የግዥ አገልግሎት ራሳችሁ ፈልጋችሁ ግዙ ብለናል።

**አዲስ ዘመን፡- ግዥ ስመፈፀም ሲባል ብቻ የቢሮ ወንበር፣ ቀለም እና የመሳሰሉትን በየዓመቱ የሚቀያይሩ አሉ። ይህ በግዥ ህግ ተገቢ ነው?**

**አቶ ሐጂ፡-** ይህን ቀለል አድርገን ብንረዳው። ለምሳሌ እኔ አሁን ያለሁበት ቢሮ ከ48 ዓመት በፊት መንግስቱ ኃይለማርያም እንደ ቢሮ ይጠቀሙበት የነበረ ሲሆን፤ የጠበቀኝ በዚያን ጊዜ የነበረ ምንጣፍ ነው። ከዚያም ወዲህ አስር ኃላፊዎች የተፈራረቁበት ምንጣፍ ላይ መቀመጥ ስላልነበረብኝ እንደአቅማችን ቢሮውን ለማስዋብ ሞክረናል። በእርግጠኝነት ግን ቀጣይ የሚመጣው ኃላፊ ይህን አያፈርሰውም። በርካታ ጊዜ ያልታደሰ ቢሮ ቢፀዳ ችግር የለውም፤ ግን በጥራት ላይ ጥራት አይመከረም። የሥራ ሥነ-ምህዳርና ቢሮ አካባቢ ቢፀዳ መልካም ነው፤ ግን በጣም የቅንጦት መሆን የለበትም። ይልቅስ እያስቸገረ ያለው በተባለው ደረጃ እና ጥራት ተሰርቷል ወይ የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-አንዳንድ ተቋማት ግዥ ስመፈፀም በተወሰኑ ተቋማት ላይ ብቻ የሚንጠለጠሉበት አሰራርስ እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ሐጂ፡-** እኔ ይህን የምረዳው በተደጋጋሚ የሚመረጡ አቅራቢዎችና ነጋዴዎች ጥቂትና የተለመዱ ናቸው የሚባለውን ከላይ ለአብነት አርሲ ዩኒቨርሲቲን አንስቻለሁ። ላለፉት ስድስት ዓመታት ግዥ በሙሉ የሚፈፀመው በሦስት ግለሰቦች የተያዘ ነው። ይህ ስህተት ነው። ዕድሉ ሰፋ ማድረግ ቢቻል ጥቅም ይገኛል። ነገር ግን በግልጽነትና በተወዳዳሪነት ብሎም ጥራትን በጠበቀ መንገድ ከሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም።

አሁን ላይ በኮንስትራክሽን ላይ የሚስተዋለው አዘግይተውና 18 ወራት ካለፈ በኋላ ዋጋ ለማስጨመር ፕሮጀክቶችን የሚያዘገዩትንና ህዝብና መንግስትን የሚያከስሩትን በሙሉ ከሲስተም እንዲወጡ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር እየሰራን ነው። በጣም ሀቀኛ የሆኑትንና በወቅቱ ያጠናቀቁትን ደግሞ ተጨማሪ ፕሮጀክት እንሰጣለን፤ ህጉን ጠብቀን። በተለይ ኮንስትራክሽን ዘገየ ማለት በጣም በርካታ ገንዘብ ያስጨምራል። ሆን ብሎ በእንዝላልነት መንግስትን ወጪ ማስወጣት ወንጀል ነው። ለአብነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት ፕሮጀክቶች በሙሉ ከተባለው ቀድመው የሚጠናቀቁ ናቸው። በዚያ መንገድ ፕሮጀክቶችን መምራት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- የግዥ ሥርዓት ላይ የሚስተዋሉ ህፀፃችን ለማስተካካል ሲባል፤ ኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ጀምራለች። ይሄ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ሐጂ፡-** ይህ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ዓለም በጣም የተጠቀመበት ነው። ይህ በየቦታው መዞርን፣ ማወቅ መተዋወቅንና ድርድርን የሚያስቀርና ቢሮ ሆኖ ማከናወን የሚያስችል ነው። በዓለም ላይ በዚህ ሥርዓት የሚጠቀሙ አገራት ከ5 እስከ 25 ከመቶ የሚሆነውን በጀታቸውን ማትረፍ ችለዋል። እኛ ሙሉ ለሙሉ ስላልጀመርን በዚህ ዓመት እቅዳችን የበጀታችንን አንድ በመቶ መቆጠብ ነው። ጨረታ የሚያወጡ ተቋማት ለጨረታ የሚያወጡት ወረቀትና ቀለም በጣም ብዙ ነው፤ በዚህ ላይ ሌሎች ደባዎች አሉ። በዚህ ሥርዓት ከቦታ ቦታ መሄድ አስገዳጅ ሳይሆን ካሉበት ቦታ ሆነው መመዝገብና መወዳደር ይቻላል። ወረቀትና ቀለም አለቀ የሚል ሰበብና የመሳሰሉትን ችግሮች ያስቀራል። የትኛውም ዓለም ክፍል ሆኖ መወዳደር ይቻላል ማለት ነው። አሰራሩ ከሙስና የፀዳ ነው። በአፍሪካ አገራት ጀምረው ስኬታማ ሆነዋል። በዚህ የተነሳ በጣም አትራፊ ነው። ግን ፈተናዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በኤሌክትሮኒክስ ግዥ የሚወዳደሩት በ€ኦንላይን‹ ነው። ስለድርጅቶች ትክክለኛነት ማረጋገጫው ምንድን ነው?**

**አቶ ሐጂ፡-** ይህ ሥርዓት ዘርፈ ብዙ ግልጋሎት የሚሰጥ ነው። ይህ ሲስተም ከንግድ ሚኒስቴር ጋር የተገናኘ ነው፤ የንግድ ፈቃድ ሙሉ መረጃዎችን የሚያሳይ ነው። በወቅቱ የሚጠበቅበትን ወቅታዊ ክፍያ ስለመክፈሉ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር ተገናኝቷል፤ የባንክ ዕዳ እንዳለበትና እንደሌለበት ከባንክ ጋር የተሳሰረ ነው። ክፍያ የሚፈፀመው በቴሌ ሲስተም በኩል ነው። ደህንነቱ እንዲጠበቅና ስትራቴጂክ ቲሙን የሚመራው ደግሞ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) ነው። ስለዚህ በዚህ ሥርዓት የተሳሰረ በመሆኑ ለማረጋገጥ ቀላል ነው። ሌላው ቀርቶ የኤሌክትሮኒክስ ፈቃድ የሌለው አካል በጨረታው ቢወዳዳር ሲስተሙ የኤሌክትሮኒክስ ፈቃድ የለውም ብሎ ያሳያል።

ባለፈው ዓመት ዘጠኝ ተቋማት በዚህ ስርዓት ግዥ ፈጽመው፤ ስድስቱ ተሳክቶላቸዋል። በዚህ ዓመት ደግሞ 63 አዳዲስ ተቋማት ወደዚህ ሥርዓት ገብተዋል። ካለፈው ዓመት ጋር 72 የፌደራል ተቋማት ይሆናሉ ማለት ነው። የቸገረን ከሚኒስቴር ጀምሮ በለመድነው ሥርዓት እንግዛ ብለው ወደ እኛ የሚመጡ አሉ። ይህ ሃሳብ የሚመጣው ከግዥ ባለሙያ ነው። ይህ የሚደረገው በአካል የሚያገኙትን ደንበኛቸውን ማግኘት ስለማይፈቅድ ነው። እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት ደግሞ መብራት ይጠፋል፤ ኢንተርኔት ይቋረጣል በሚል ነው። እኛም በኦንላይን ግዥ፣ ጨረታ ማውጣትንና ውል ማስተዳደር የመሳሰሉትን አስመልክቶ ለተቋማት ስልጠና እየሰጠን ነው። አሁን የቀረን አቅራቢዎች ላይ ነው። እስከ አሁን 3000 የሚሆኑ አቅራቢዎች ተመዝግበዋል። በአገሪቱ ያለው አቅራቢ ከዚህ በላይ ነው።

ከታህሳስ ጀምሮ በኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ያልተመዘገበ አቅራቢ በማንኛውም ጨረታ ላይ መሳተፍ አይችልም። ለዚህ ደግሞ ተቋማችን ስልጠና ይሰጣል። በዚህ ሳምንት 1000 አቅራቢዎችን ጠርተን እናሰለጥናለን። ከዚህ በፊትም ሁለት ጊዜ ሞክረናል፤ ግን የሚመጣው ሰው በቀጥታ የማይመለከተው ነው። ከአሁን በኋላ በየሱቁ እየዞሩ መግዛት ሙሉ ለሙሉ ያቆማል። በዚህ ሲስተም የማይደሰቱ የግዥ ሰዎች አሉ። ምክንያቱም ድሮ እንደለመዱት የሻይ ቡና የሚባል ነገር ይቀርባቸዋል። የኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ይህን ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ ያስቀራል።

በሁለተኛው ዙር 51 የፌደራል ተቋማት ወደዚህ ሲስተም ይገባሉ። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስተቀር በ2015 ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ወደዚህ ሲስተም ይገባሉ። ሲስተሙ በ40 ዩኒቨርሲቲዎች ይዘረጋል። በእርግጠኝነት በዚህ ዓመት መጨረሻ ከዩኒቨርሲቲዎች በስተቀር ሁሉም የፌደራል ተቋማት በኤሌክትሮኒክስ ሲስተም የሚከናወን ሥርዓት ውስጥ ይገባሉ። በመሆኑም በ2016 ዓ.ም አቅራቢዎቻችን በዚህ ደረጃ ዘምነው መገኘት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ቀድሞ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት በዘረጉት ስድስት ተቋማት ምን ለውጥ ተገኘ?**

**አቶ ሐጂ፡-** ሥርዓቱን በተገበሩ ስድስቱ ተቋማት የወረቀትና ቀለም ብክነት እንዲሁም ሙስና ቀርቷል። ብዙ ሃብት መቆጠብ ተችሏል። የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በቴክኒክ የሚመራው እሱ ነው፤ ቀደም ብሎ ወደ ሲስተሙ ስለገባ ተጠቅሟል። እቅድም የሚያቀርበው በዚህ ነው። በዚህ ዓመት 100 የሚሆኑ የፌደራል ተቋማት እቅዳቸውን ያቀረቡትም በዚሁ ሲስተም ነው። በርካታ ተቋማት ወደ ሲስተሙ ለመግባት ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ ነው። እኛም ሲስተሙን ስንተገብር ከአገሪቱ 761 ቢሊዮን ብር በጀት ውስጥ አንድ ከመቶ እናድናለን ብለን እየሠራን ነው። ከሌብነትና ንክኪም የፀዳ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ተጨማሪ ሐሳብ አልዎት?**

**አቶ ሐጂ፡-** የክልልም ይሁን የፌደራል ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ግዥ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን መረዳት አለባቸው። ግዥ ለግዥ ባለሙያ ብቻ አይተውም፤ የበላይ ኃላፊዎች ክትትልና ትኩረት ይፈልጋል። የግዥ እቅድ የሌላችሁ ተቋማት ያላችሁት ሌብነት ውስጥ ነው። የግዥ እቅድ ሳይኖር ግዥ መፈፀም ደረቅ ወንጀል ነው። ማንኛውም ተቋም ያለእቅድ ግዥ ቢፈጽም ህገ-ወጥ ነው። አጥብቀን እንከታተላለን፤ ለፓርላማም እናሳውቃለን። ገንዘብ ሚኒስቴርም በጀት መከልከል እንደሚችል እናሳያለን። ሚዲያዎችም በዚህ ደረጃ መሥራት አለባቸው። እቅድ የሌላቸውን 60 የፌደራል ተቋማት ስለምናሳውቅ መጠየቅ ይጠበቅባችኋል።

ሌላው በርካታ ተቋማት የሚያነሱት የተሸከርካሪ እጥረት ነው። አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ ይታያል። መንግስት ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ነው። ባለፈው ዓመትም በጦርነት ውስጥ ስለነበርን የመኪና ግዥ አልተፈፀመም። በዚህ ዓመት ግን አቅም በፈቀደ መጠን ግዥ ተፈፅሞ ይሰራጫል። በመጨረሻም የተቋም ኃላፊዎች ከተመደበው በጀት 70 ከመቶ ለግዥ የሚውልን ሃብት በመሆኑ ያለዕቅድ ግዥ መፈጸም ቀጥታ ሙስና መሆኑን ማስታወስ እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፤ ለቀይታችን አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሐጂ፤** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ስምስም መሬት፤ ታይቶ የማይጠገብ መልከዓ-ምድር፤ የዋህና እንግዳ አክባሪ ህዝብ ...


ካብታሙ አየለ (ረዳት ፕሮፌሰር)

## የፈታኙ ማስታወሻ

ካብታሙ አየለ (ረዳት ፕሮፌሰር፤ አርሲ ዩኒቨርሲቲ)
ኢሜይል: kabayjim8@gmail.com

የ2014/15 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በዩኒቨርሲቲዎች ይሰጣል የሚል ወሬ የተሰማው ቀደም ብሎ ነበር። ከወሬ አልፎ ተግባራዊ ይደረጋል የሚል እምነት አልነበረኝም። ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ተማሪዎችን ወደ በዩኒቨርሲቲ ማጓጓዝና መመገብ ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል። ከገንዘቡም በላይ አፈፃፀሙ የዩኒቨርሲቲዎችን አቅም እንደሚፈትን መገመት አያዳግትም። የትምህርት ሚኒስቴር "ከመስከረም 20 እስከ ጥቅምት አጋማሽ በዩኒቨርሲቲዎች ግቢ ውስጥ ምንም ተማሪ እንዳይኖር" የሚል መመሪያ ማስተላለፉን ስሰማ እንኳን የምር ተግባራዊ ይደረጋል ብዬ አላመንኩም። ብዙም ሳይቆይ "ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ሄዳችሁ መፈተን የምትፈልጉ መምህራን በየትምህርት ክፍላችሁ ተመዝገቡ" የሚል ጥሪ ሲመጣ ጉዳዩ ቁርጥ መሆኑን ለማመን ተገደድኩ። አንድ የስራ ባልደረባዬ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደማስብ ሲጠይቀኝ እንዲህ ብዬ መለስኩለት።

"እኔ ወታደር አይደለሁም። ዘምቼ ሀገሬን አሁን ከሚወጓት የውጭና የውስጥ ጠላቶች ልጠብቃት አልችልም። ገበሬ ሆኜ ሰብል በማምረት ወገኖቼን አልቀልብም። ጥበበኛ ሆኜም በጥበብ የሀገሬን ስም አላስጠራም። እኔ መምህር ነኝ። ለሀገሬ አስተዋፅኦ ላበረክት የምችለው በሙያዬ ነው። ሙያዬ የሚጠይቀውን ግዴታ ለመወጣት ዝግጁ ነኝ። መንግስት ጥበቃ እንዲያደርግልኝ፤ ምግብና መኝታ እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ። በተረፈ የተመደብኩበት ቦታ ሄጄ ልፈትን ዝግጁ ነኝ" አልኩት። ጓደኛዬም አቋሙ ከእኔ ጋር ተመሳሳይ ነው። በብዙ ሀገራዊ ጉዳዩች ዙሪያ ተቀራራቢ አቋም አለን። የተሰጠንን ፎርም ሞልተን ለመመለስ ጊዜ አልወሰደብንም።

ከሳምንታት ቆይታ በኋላ ተማሪዎች የሚፈተኑበት ዩኒቨርሲቲ ግልፅ ተደረገ። በዚህ ወቅት እኛም የምንፈትንበትን ዩኒቨርሲቲ ለማወቅ ጓጓን። እንዲያውም የእኛ ምደባ በመዘግየቱ ቅሬታ ተሰማን ማለት ይቻላል። ምደባው በመዘግየቱ የየግል ጉዳዮቻችንን ለማስቀድም ተቸገርን። ቀኑ እየቀረበ ሲሄድ "በምናስተምርበት ዩኒቨርሲቲ እንድንፈትን ፈልገው ይሆናል" የሚል ጥርጣሬ አደረብን።

ከእለታት በአንዱ ምሽት ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሣይንስ ተማሪዎችን እንድፈትን መመደቤን የሚገልጽ መልዕክት በእጅ ስልኬ በኩል ደረሰኝ። ደነገጥኩ። መልዕክቱን ደጋግሜ አነበብኩት። ምንም የተለየ ነገር ለውም። እድሜ ለቴክኖሎጂ! የሚዛን ቴፒን ርቀትና የተለያዩ መረጃዎች ከድህረ-ገፅ አስሼ አገኘሁ። በማግስቱ ወደ ቢሬ ሄጄ የስራ ባልደረቦቼ የት እንደደረሳቸው ጠየኳቸው። አብዛኞቹ ሃዋሳ፤ ወላይታ ሶዶ፤ ባህር ዳር፤ ጎንደር፤ ደብረማርቆስ፤ ዲላና የመሳሰሉት ዩኒቨርሲቲዎች እንደ ደረሳቸው ነገሩኝ። ደስታና ቅሬታ ተምታቱብኝ። ከዚህ በፊት ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ሲያስተምር ወደ ነበረ የስራ ባልደረባዬ ስልክ ደወልኩና ሁኔታውን ነገርኩት።

"አገሩ በጣም ጥሩ ነው። ይህን አጋጣሚ ዳግም ስለማታገኘው ሄደህ ኢትዮጵያን አይተህ ተመለስ" አለኝ። አጭርና ልብ አንጠልጣይ ምክር ነበር። የበለጠ ተበረታታሁ። ስለአካባቢው ለማወቅ ፈልጌ እንጂ ለመቅረት አስቤ እንኳን አልነበረም። ራሴን እስከማውቀው ድረስ ከሀገር ጥሪ የምቀር ሰው አይደለሁም። ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ "ሄደህ ኢትዮጵያን እይ! የሚለኝ ምን የተለየ ነገር ቢኖር ነው?" የሚል ጥያቄ በውስጤ ተፈጠረ። እስከ ጂማ ድረስ በአውሮፕላን መሄድ እንደምችል ባውቅም ጉዞዬን በአውቶቡስ ለማድረግ ወሰንኩ። አጭር የአውሮፕላን ጉዞ ምቾትና ፍጥነት እንጂ ቀሪ ትዝታ እንደሌለው አውቃለሁ። ጥቂት ቅያሬ ልብሶችና የሚነበቡ መፅሃፍትን ይዤ አዳሬን አዲስ አበባ አደረኩ።

ጎህ ሣይቀድ ላምበረት አካባቢ ከሚገኘው የአውቶቡሶች ማደሪያ ተነስተን ጉዟችንን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አደረግን። በትዝታ መነፅር 23 ዓመታትን ወደ ኋላ ተመለስኩና በብቸኛው ዋሊያ አውቶቡስ ከሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ ጋምቤላ የገባሁበትን ጊዜ አስታወስኩ። መንገዱ እንደ አሁኑ ቀላል አልነበረም። ከአዲስ አበባ በመነሳት ጂማ ይታደራል። የሁለተኛው ቀን አዳር መቱ ይሆናል። በሶስተኛው ቀን ከስምንት ሰዓት ጉዞ በኋላ ጋምቤላ ይገባል። ታዲያ ለዚህ ሁሉ ጉዞ ክፍያው ሶስት መቶ ብር እንኳን የሚሞላ አይመስለኝም።

ፀሐይ በአናታችን ትይዩ ስትሆን ምሳችንን በአባ ጁፋር አገር ጂማ በልተን ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ዞርን። እንደ ድሮው "ይህቺ ከተማ ምን ትባላለች?" እያልኩ ሰው መጠየቅ፤ የንግድ ባንክ ፅሁፍ ማየት ወይም የትምህርት ቤት ታፔላ ላይ ማፍጠጥ አላስፈለገኝም። ስልኬን በቀጥታ ቦታ ጠቋሚ (Live Location) ላይ አድርጌ በእጄ መደንቀል ብቻ በቂ ነበር። ስልኬ ሰቃ፤ ሸቤ፤ አሚዮን እያለ የቦታዎችን ስም ይዘረዝርልኛል። ልክ ሰቃን እንዳለፍን የተለየ መልከዓ-ምድር ተቀበለን። ወደ ቀኝ፤ ወደ ግራ፤ ወደፊት ሲታይ ሁሉም ነገር አረንጓዴ ነው። ጥብቅ የተፈጥሮ ደን መሰሎኝ ነበር። ነገር ግን በየዛፉ ጥግ ቤትና የቤት እንስሳት፤ ራቅ ብሎም የእርሻ ማሳዎች ይታያሉ። የተለየ ፓርክ ሳይሆን ነዋሪ የጠበቀው የተፈጥሮ ደን መሆኑን አወቅሁ።

የአካባቢው ማህበረሰብ ከደን ጋር ያለው ህብረት ያስገርማል። ደን ሳይመነጥር በስሩ ቤት ይሰራል፤ ቡና ይተከላል። ከአረንጓዴ ዛፎች ጋር በጉርብታና ይኖራል። ዛፎች ከዕለት-ተዕለት ኑሯቸው ጋር ተቆራኝተዋል። እንደ ኮሶ፤ ዋርካና ዝግባ ዛፎች አይን ይማርካሉ። ሌላ ቦታ በብዛት የማይታዩ ናቸው። ከማድነቅም በላይ ስጋት ገባኝ። ጂማ ከተማ ውስጥ በየበረንዳው ተዘርግተው የሚቸበቸቡ የእንጨት ኩርሲዎችን፤ ትንንሽ ተሰኪ ጠረጴዛዎችንና የእንጨት ጌጣጌጦችን ያየ ሰው "የዚህ ደን እጣ ፈንታ ምን ይሆን?" ብሎ መስጋቱ ተገቢ ይመስለኛል።

የቀን ውሎዬን የመመዝገብ (dairy keeping) ልምድ ባይኖረኝም ይህን መሰል ፀጋ እያየሁ ማለፍ ግን ከበደኝ። የኪሴ ማስታወሻዬን አውጥቼ "ምድር ሳትራብ ሰዎች ለምን ይራባሉ?" ብዬ ፃፍኩ። ማንን እንደምጠይቅ እንኳን አላውቅም። ይሄን ሁሉ ፀጋ እያለን ለምን ተራብን የሚል ቁጭት ተናነቀኝ። ሸቤንና አሚዮንን እያቆራረጥን ወደ ቦንጋ ቀረብን። አውቶቡሳችን ምድራዊ አውሮፕላን ነው ማለት ይቻላል። በእርጋታ ቢሄድ አካባቢውን በደንብ አይ ነበር ስል በመኪናው ፍጥነት ቅሬታ ተሰማኝ። ወደ ቦንጋ ስንጠጋ ጎጀብ ወንዝ ከነግርማ ሞገሱ ተቀበለን። ያስፈራል።

እርሱም እንደ ሌሎች ወንድሞቹ ለም አፈራችንን ጭኖ እየተጣደፈ ነው። አባይ፤ ባሮና ዋቤ ሸበሌን በደንብ አውቃቸዋለሁ። ጎጀብም ከእነርሱ እንደ አንዱ ከቤቱ አፈር ጭኖ ለባዕድ ሊያቀብል ይሮጣል። አለመታደል ሆኖ ወንዞቻችን ሀገራቸውን በዳይ፤ የባዕድ ሲሳይ ናቸው። ከሁሉ በላይ የሚያበሳጨው አፈራችንን ጭነው መሄዳቸው ነው። ጎጃብ ወንዝም ደፍርሶ የሚሄደው ያው ለም አፈራችንን ጭኖ ነው። ተረጋግቼ ለማሰብ እንኳን ጊዜ ሳላገኝ መኪናው በፍጥነት አሳለፈኝ።

"እንኳን ወደ ቡና መገኛ ምድር ወደ ከፋ በሰላም መጣችሁ" የሚል ፅሁፍ የያዘ ታፔላ በጨረፍታ አነበብኩ። አውቶቡሱ ከንፋስ ጋር ፉክክር የገጠመ ይመስል ፍጥነቱ ወደ ውጭ ለማየትና ለማንበብ ጊዜ አይሰጥም። በዚህ ቅፅበት ሌላ ነገር ትዝ አለኝ። ለካ የሰው ዘር መገኛ ብቻ ሳንሆን የቡናም መገኛም ነን አልኩኝ። ግን ደግሞ "መገኛ" ብቻ መሆን ምን ዋጋ አለው? የሰው ልጅ መገኛ የሆነችው ሀገራችን ዛሬ የሰው ልጅ የሚራብባት ምድር ሆናለች። የቡና መገኛ ብንሆንም ከቡናችን ምን ያህል እየተጠቀምን ነው? እያልኩ ከራሴ ጋር ሙግት ገጠምኩ።

ብዙም ሳንርቅ ጉም እይታችንን ገደበው። በማን እንደምበሳጭ ባለውቅም ተበሳጨሁ። አንዳንድ ተሳፋሪዎችን እንቅልፍ ከወንበር ጋር ያላትማቸዋል። አንዳንድ ወጣት መንገደኞች ደግሞ ለጓደኞቻቸው እየደወሉ የቦታውን ርቀት ያማርራሉ። ርቀቱ እንጂ ልምላሜው ለምን እንዳልታያቸው እኔ አላውቅም። አልፈርድባቸውም። እኔም የዛሬ 23 ዓመት የኢሉባቦርን ጥቅጥቅ ደኖች አቋርጬ ስሄድ የሚታየኝ ርቀቱ ብቻ ነበር። ይኼ የሁላችንም ችግር ነው። ማንቀላፋት ፀጋዎቻችንን እንዳናይ መጋረጃ ሆኖብናል። የሚጎድለንን ብቻ እያሰብን ማማረር ያለንን ሀብት እንዳናይ ከልሎናል።

አመሻሹ ላይ ሚዛን ገባን። የተያዘልን መኝታ ጥሩ አልነበረም። ያንንም የያዘችልኝ ከእኔ በሰዓታት ቀድማ የደረሰች የስራ ባልደረባዬ ነበረች። እንደምንም አድረን በማግስቱ የተሻለ መኝታ ያዝን። መታጠቢያውና መፀዳጃው ከክፍሉ ውጭ ቢሆንም ንፁህ ነው። ከቤት የወጣነው ለአገራዊ ተልዕኮ እንጂ ለቅንጦት ስላልሆነ መመፃደቅ እንዳሌለብን እናውቃለን። የዚህ ፅሁፍ ዓላማም የጎደለውን በማንሳት ማማረር ሳይሆን የአካባቢውን ውብ ተፈጥሮ ማሳየትና ያላዩት ሄደው እንዲያዩ ማነሳሳት ነው። የከተማው መሬት አቀማመጥ ኮረብታና ሸለቆ ይበዛዋል። ቢሆንም ግን ዋና መንገዱን ተከትሎ ብዙ ዘመናዊ ህንፃዎች ተገንብተዋል። በዚህ ርቀት ላይ እነዚህን የመሰሉ ዘመናዊ ህንፃች ይኖራሉ ብዬ አላሰብኩም። ቁርስ የት እንደሚገኝ ስንጠይቅ ስጋ ቤቶቹን አሳዩን። ሚዛን ላይ ስጋ በፍቅር ይበላል።

አስተናጋጁ ወደ እኛ ሲጠጋ "ለእንግዳ የሚሆን ቁርስ ምን አለ?" አለችው። ከእኔ ቀድማ ሚዛን የገባችዋ መምህርት ነበረች። የመምህርቷ ድፍረትና ጠያቂነት ያስገርማል። ማወቅ የፈለገችውን ነገር ሁሉ ትጠይቃለች፤ ነካክታ ታያለች። አንዳንዱን ቀምሳም ትሞክራለች። ወደ ዩኒቨርሲቲው ስንሄድና ስንመለስ የዩኒቨርሲቲው ሎጂስክ ኃላፊ ዘንድ ደውላ መኪና የምታስመጣልን እርሷ ነበረች። ከሰው መግባባትና ድፍረትን ከታደሉት ሰዎች አንዷ ናት ማለት እችላለሁ።

"ማቾኒ ይሁንላችሁ?" አለን ። እኛ የጠበቅነው "ምላስ ሰንበር"፤ "ዱለት ወይም ቁርጥ" የሚል ነበር። "አዎ ይሁን!" አልን ምንነቱን ሳናውቅ። መቼም የተሻለ ነገር ቢሆን ነው የመረጠልን ከሚል እሳቤ ነው። "ማቾኒ" በዳቃቅ የተከተፈ ስጋ ጥብስ ነው። በሚያምር መጥበሻ በበቆሎ እንጀራ ተሸፋፍኖ መጣልን። በዳጣ እያጠቀስን አጣጣምነው። ዋጋውም ተመጣጣኝ ነው። ከዚያ በኋላ ከሚዛን እስከወጣን ድረስ "ማቾኒ" የእለት ምግባችን ሆኖ ቀረ። የምግቡ ጣዕም ብቻ ሳይሆን ስሙም ለጆሯችን ጣመን። ማቾኒ !

አቅጣጫውን ከጠየቅን በኋላ ታክሲ ተሳፍረን ወደ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ አመራን። ግቢውን ተዘዋውረን አልጎበኘንም። መማሪያ ክፍሎችና ቢሮዎች አካባቢ ብቻ በስራ ምክንያት ተዘዋወርን። አባጣ-ጎባጣ በበዛበት መሬት ላይ አስገራሚ ህንፃዎች ተሰርተዋል። አንድ ቦታ ላይ ረጅምና ተያያዥ የሆነ ህንፃ ተገንብቷል። በዚህ ርቀት ይሄን የመሰል የህንፃ ዲዛይን አይቶ አለማድነቅ ንፉግነት ነው። ሕንፃው ያረፈበት መሬት ከአንድ የእግር ኳስ ሜዳ አይተናነስም። የተወሰኑ መማሪያ ክፍሎችን በስተቀር ሌሎቹ ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ አላየሁም። "ምን አለ ቢያስጎበኙን?" ማለቴ አልቀረም። ምናልባትም እኔ ከሄድኩ በኋላ ቀሪዎቹን ፈታኞች አስጎብኝተው ሊሆን ይችላል።

ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች አይተን የማናውቀው የተፈጥሮ ስጦታ አለው። አንድ ትልቅ ወንዝ ግቢውን ሁለት ቦታ ከፍሎ ያልፋል። ከአስተዳደር ቢሮዎች ወይም ከአዲሱ ህንፃ ወደ ተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ለመሄድ ወንዙን ማለፍ ግድ ነው። የመጀመሪያው ቀን ሁላችንም ተገርመን ቆመን አየን። ውሃው ከአለት ጋር እየተላተመ ሲወርድ የሚፈጥረው ድምፅ መንፈስን ያድሳል። ተፈጥሮ ያለገደብ ሲሰጥ እንደዚህ ነው። አብሮኝ ለነበረው ጓደኛዬ እንዲህ አልኩት። "ተፈጥሮን ለማድነቅ ከቻልክ ሚዛን ተወለድ፤ ካልቻልክ ደግሞ ሚዛንን ጎብኝ" አልኩት። ተሳስቀን ወደ ጉዳያችን ሄድን።

መመገቢያ አዳራሹ ፊት የተሰለፉ ተማሪዎች ከሙብዛታቸው የተነሳ ጠጠር ቢወረወር መሬት አያርፍም። እነዚህን ተማሪዎች መመገብና ማቆየት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ሳስብው ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ያለኝ አክብሮት ጨመረ። በሰልፉ መሃል አቆራርጠን አልፈን መፈተኛ ክፍላችንን አገኘን። የተወሰነ ኦረንቴሽን ወስደን ወንበሮችን አስተካክለን ተለያየን።

ከዋናው ግቢ ከ3 ኪሎ ሜትር ባልበለጠ ርቀት አማን የሚባል ቦታ አለ። የዩኒቨርሲቲው ጤና ሣይንስ ኮሌጅ የሚገኝበት ክፍለ-ከተማ ነው። ከኮሌጁ ፊት ለፊት አንድ ሰፊ ሜዳ አየን። እስከ አሁን ካየነው የመሬት አቀማመጥ ይህን የመሰለ ሜዳ መኖሩ ገረመንና አብሮን የነበረውን የአካባቢውን ተወላጅ ጠየቅነው። "ይሄ የድሮ አየር ማረፊያ ነው። አባቶቻችን በእጃቸው ቆፍረው የገነቡት አየር ማረፊያ ነበር። ግንባታ እንዳይካሄድበት የከለከለው የአካባቢው ማህበረሰብ ነው። አባቶቻችን ከገጠር ሳይቀር ስንቅ ይዘው መጥተው ሳምንታትን እዚህ ቆይተው ነው የሰሩት።

ለልጆቻችን መጫወቻ ይሆናል እንጂ ግንባታ አይካሄድበትም ብለው ነው የከለከሉት" አለን። "ምናለ ሁሉም ሰው እንደዚህ ቢያስብ?" አልኩኝ። እኔ እንኳን የማውቃቸው የጎባና የአሰላ የድሮ አየር ማረፊያ ቦታዎች እንዲህ የሚጠብቃቸው ሰው አጥተው ነው የተወረሩት። እነዚህ ከተሞች አሁን አየር ማረፊያ የላቸውም። በቅድመ-ስልጣኔ የነበሩ አባቶችን ያህል ማሰብ ያቃተን ትውልድ ስለመሆናችን ማረጋገጫው እንደዚህ ዓይነት ተግባር ነው። እነርሱ ግሬደርና ዶዘር ባልነበረበት ዘመን በእጃቸው መሬት ቆፍረው፤ በትከሻቸው አፈር ተሸክመው የሰሩትን እኛ ተማርን የምንል ልጆቻቸው ለጎጆ መስሪያ ቸረቸርነው። ሚዛን-አማን ላይ ግን ይሄ አልሆነም። አውሮፕላን ባያርፍበትም ልጆች ኳስ ይጫወቱበታል፤ ስፖርት ይሰሩበታል።

በፈተናው ዕለት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል በየክፍላችን መገኘት እንዳለብን ተነግሮናል። ምግብ ቤቶች በጠዋት እንደማይከፈቱ ስለገባን ማታውኑ ሙዝ፤ አቮካዶና ዳቦ ገዛዝታን ወደ ማደሪያ ክፍላችን ሄድን። በጣም ቀላል፤ ነገር ግን ትልቅ ሃላፊነት ይጠብቀናል። ምንም እንኳን የድካም ስሜት ባይሰማኝም በጊዜ ተኛሁ። ነገር ግን ንጋት ላይ እንቅልፍ አልወስደኝ አለ። ደግነቱ የሚነበብ መፅሐፍት ስለያዝኩ አልጋ ላይ መገላበጥ አላስፈለገኝም።

ከተባለው ሰዓት ቀድመን በየመፈተኛ ክፍላችን ተገኘን። የተፈታኞችን የመመዝገቢያ ቁጥር እያየን ወደ ክፍል አስገብተን በተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ አስቀመጥናቸው። በየወንበራቸው ላይ የመመዝገቢያ ቁጥራቸውን ፅፈን ስለነበር በእጃቸው የያዙትን ካርድ ከተፃፈው ቁጥር ጋር እያመሳከርን አረጋገጥን። ሱፐርቫይዘሩ መልስ መስጫ ወረቀቶችን አምጥቶ ሰጠኝ። ለሌሎች ፈታኞችም ሰጥቶ መምጣቱን አውቃለሁ። ልክ እንደ ጥያቄ ወረቀቱ ግራና ቀኝ እያልኩ ለሁሉም ተፈታኝ አደልኩ። ከስማቸው በመጀመር ሌሎች መሞላት የሚገባቸውን መጠይቆች እንዲሞሉ አደረኩ።

ሱፐርቫይዘሩ ሁለት የታሸጉ ፖስታዎችን አምጥቶ ሰጠኝ። የጥያቄ ወረቀት ነበር። ፖስታው የታሸገ መሆኑን በማሳየት በእነርሱ ፊት ከፍቼ ጥያቄ ወረቀቱን በጥንቃቄ አደልኳቸው። ሰዓቱ እስኪደርስ በመጀመሪያው ገፅ ላይ የተፃፈውን አጠቃላይ መመሪያ እያነበቡ እንዲቆዩ አደረኩ። ገፁን ገልጠው ጥያቄዎቹን ለማየት የሚሞክሩ ተማሪዎችን እየተከታተልኩ አስቆምኳቸው። ብዙም አላስቸገሩኝም። ልክ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን ተደወለና ፈተናው ተጀመረ። ዋናው ስራ ከዚህ በኋላ ነበር። መቆጣጠር።

አጠገባቸው ካለው ተማሪ ጋር ለማውራት መሞከር፤ ማንሾካሾክና አጮልቆ ወደ ሌላ ተማሪ ለማየት የሚደረጉ ሙከራዎች ነበሩ። በምልክት ወይም አጠገባቸው ሄጄ ሳስጠነቅቃቸው ወዲያው ከድርጊታቸው ይታቀቡ ነበር። እኔ ቋንቋቸውን አልችልም። እነርሱ አማርኛ በመጠኑ ይሰማሉ። መግባባት ግን አላቃተንም። ትንሽ ለየት ያለ ድርጊት ሳይ አጠገባቸው ሄጄ ቆም እላለሁ። ቀና ብለው ያዩኛል። በጣቴ የማስጠንቀቂያ ምልክት እሰጣቸዋለሁ። አይናቸውን ወደጥያቄቸው ይመልሳሉ። በቃ ! ቀና ብለው እንኳን አያዩም።

በበኩሌ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የፈተንኩት ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ነበር። በወቅቱ ከፈተና ጋር የተገናኘ የስነ-ምግባር ጉድለት እንደ አሁኑ የከፋ አልነበረም። አሁን ያለውን የፈተና ሁኔታ ከሰው ከመስማት ባለፈ በተግባር የማውቀው ነገር አልነበረም። በዚህ ምክንያት ተማሪዎች በጣም ሊያስቸግሩኝ ይችላሉ የሚል አመለካከት ይዤ ነበር የሄድኩት። ተማሪ ቢያስቸግር ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ። ከአስር ዓመታት በላይ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ሳስተምር ከፈተና አወጣጥና አፈታተን ጋር የተገናኙ ኮርሶችን እሰጥ ነበር። በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎችን ስፈትን የጠበኩትን ዓይነት የስነ-ምግባር ጉድለት አላየሁም። አብረውኝ የነበሩት ፈታኞችም ችግር መኖሩን ሲያወሩ አልሰማሁም።

መጥፎ ድርጊት ስናይ እንደምናወግዘው ሁሉ ጥሩ ነገር ስናይ ማመስገን መልመድ አለብን። እኔ የፈተንኳቸው ተማሪዎች ከዳውሮ ዞን ገሳ ዳልባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡ ነበሩ። በፈተናው ወቅት ላሳዩኝ መታዘዝና ከበሬታ ከልቤ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። በማስተምርበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ፈተና ስሰጥ የማያቸውን የፈተና ስነ-ስርዓት ጥሰቶች የሚያህል እንኳን አላየሁም። ይሄን ማየቴ ከመገረምም አልፌ ተስፋ እንዲኖረኝ ረድቶኛል።


ብሔራዊ ፈተናን እንደ ቅርጫ ስጋ ሁሉም ተማሪ የሚጋራበት ዘመን ላይ መድረሳችን የማያሳዝነው ሰው ያለ አይመስለኝም። በዚህ ዓመት ይህን ጸያፍ ተግባር ለማስቀረት የተደረገው ጥረት የሚበረታታ ነው። በበኩሌ የችግሩ ዋና ተዋናይ ተማሪዎች አለመሆናቸውን ከዚህ ፈተና ተገንዝቤያለሁ። የትምህርት ቤት አስተዳደር፤ መምህራን፤ ወላጆች፤ በየደራጃው ያለ የመንግስት መዋቅር ሁሉም ራሱን መጠየቅ ያለበት ይመስለኛል።

ወደ ሚዛን ቴፒ ስሄድ በጥርጣሬና በስጋት ነበር። ስመለስ ደግሞ በተስፋና በቁጭት ሆነ። መጀመሪያውንስ ለምን ነበር ስጋትና ጥርጣሬ ያደረብኝ? በ20ዎቹ መጀመሪያ ዕድሜዬ ጋምቤላ ድረስ የሄድኩት ሰውዬ ዛሬ ምን ሆኜ ነው ሚዛን መሄድ ያስፈራኝ? ኧረ ለመሆኑ ማነው እንዲህ እንድንፈራራ ያደረገን? ሚዛን ቴፒ የሚናፈቅ መልከዓ-ምድር፤ የሚወደድ ሰው እንጂ የሚፈራ ምንም ነገር እንደሌለ ማርና ቡናውን የቀመሰ ይመሰክራል። እኔ አንዱ ምስክር ነኝ።

በዘንድሮው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ምክንያት ለምለም መሬት፤ ታይቶ የማይጠገብ መልከዓ-ምድር፤ የዋህና እንግዳ አክባሪ ህዝብ ...ተመልክቻለሁ። ሙያዊ ግዴታዬን ለመወጣት ብዬ በስጋት የሄድኩበት ቦታ የሀገሬን ተስፋ ተረድቻለሁ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኜ ኢትዮጵያን ጎብኝቼ፤ ትልቅ ተስፋ ሰንቄ ተመልሻለሁ። በስጋት ሄጄ በተስፋና በትዝታ ወደ ቤቴ ገብቻለሁ። አመሰግናለሁ የሚዛን ወገኖቼ። አመሰግናለሁ የገሳ ዳልባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች። ገለታይ! አበቃሁ!

# ከኮሜርሻል ወደ ስፔሻሊቲ ቡና

ኃይሉ ሣህለድንግል



ሀገሪቱ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ስፔሻሊት ቡና እየጨመረ እንዲሄድ ጥራት ላይ በትኩረት መስረቷ መቀጠል አለበት

ኢትዮጵያ ቡና ለአለም ገበያ በማቅረብ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ ባለፉት አመታት እየጨመረ መጥቷል። ባለፈው በጀት አመት ብቻ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል። ይህን ያህል መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ የተገኘው በበጀት አመቱ 300 ሺ ቶን ቡና በመላክ ሲሆን፣ ገቢውም ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ታሪክ የመጀመሪያው ለመባል በቅቷል።

ሀገሪቱ ከዘርፉ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ እያገኘች ቢሆንም፣ ያላት እምቅ አቅም ከዚህም በላይ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት እንደሚያስችላት የዘርፉ አካላት ይጠቁማሉ። በተለይ በቡና ጥራት በተለይም በስፔሻሊቲ ቡና አቅርቦት ላይ አተኩራ ብትሰራ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ ልትሆን እንደምትችል መረጃዎች ያመለክታሉ።

ለገበያ የሚቀርብ ቡና የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፣ እስከ ደረጃ ሶስት ያሉት ስፔሻሊቲ ቡና፣ አራተኛና አምስተኛ ደረጃዎቹ ደግሞ ኮሜርሻል ቡና በመባል ይታወቃሉ። ሀገሪቱ ለዓለም ገበያ ከምታቀርበው ቡና አብዛኛውን እጅ የሚይዘው ኮሜርሻሊቲ ቡና ሲሆን፣ የተቀረው ስፔሻሊቲ ቡና ነው።

ኢትዮጵያም ከዚህ የቡና ግብይት ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ለውጭ ገበያ በምትልከው ቡና ጥራት ላይ አተኩራ መስራት እንዳለባት በእጅጉ ታምኖበታል። የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ ባለፈው ነሐሴ ወር ለንባብ በበቃው የባለስልጣኑ መጽሄት ላይ ሀገሪቱ ለዘመናት ስትጠቀምበት በቆየችበት መንገድ ኮሜርሻል ቡናዎችን ብቻ እየላከች ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም ሲሉ ያስገነዘቡትም ይህንኑ ያመለክታል፤ ዋና ዳይሬክተሩ ከዚህ የቁጥ ቁጥ ገቢም መላቀቅ እንዳለባት በጥናት መገንዘብ መቻሉንም ነው ያስገነዘቡት። ‹‹ከዚህ ወጣ ብለን አይናችንን ከፊት አድርገን የስፔሻሊቲ ቡና ገበያን ማማተር ይኖርብናል›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ከቡና ገዢዎቻችን አብዛኛዎቹ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ከተለመደው የቡና ቃና ወጣ ብለው ማጣጣም ይፈልጋሉ ሲሉም ያብራራሉ።

ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘው እንዳመለከቱትም፤ ኢትዮጵያ እኤአ ከ2015 እስከ 2017 ለዓለም ገበያ ያቀረበችው ኮሜርሻል ቡና 4፣ 5 እና ዩጂ ደረጃ የነበረው ሲሆን፣ የገበያ ድርሻውም 66 በመቶ ነው። ይህ ቡናም በኪሎ ግራም እስከ 1 ነጥብ 06 የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነው የተሸጠው። በአንጻሩ ደረጃ 1፣2፣3 ያላቸው ቡናዎች ግን 34 በመቶ ብቻ የገበያ ድርሻ ነው ያላቸው። እነዚህ ቡናዎች የተሸጡበት ዋጋ ግን በኪሎ ግራም በአማካይ ከ2ነጥብ39 እስከ 2ነጥብ 66 የአሜሪካ ዶላር ነው። በቀላል ምሳሌ 1000 ኪሎ ግራም ኮሜርሻል ቡና ተልኮ የተገኘው አንድ ሺ ስልሳ ዶላር፣ 400 ኪሎ ግራም ተልኮ ከሚገኘው የስፔሻሊቲ ቡና ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ነው። በእነዚህ መካከል የ600 ኪሎ ግራም ቡና ልዩነት ይታያል። በጥራት የተመረቱት ደረጃ 1፣2፣3 ቡናዎች፣ ከደረጃ 4፣5 እና ከዚያ በታች ከሆኑት ከእጥፍ በላይ የዋጋ ልዩነት ያሳያል።

የተጠቀሱት መረጃዎች በስፔሻሊቲ ቡና ላይ በትኩረት የመስራትን አስፈላጊነት በሚገባ ያመለክታሉ። በኮሜርሻልና ስፔሻሊቲ ቡናና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያነጋገርናቸው የቡናና ሻይ ባለስልጣን የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር አቶ ታጠቅ ግርማ በስፔሻሊቲ ቡና ላይ ለውጥ እየታየ መሆኑን ይገልጻሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የዛሬ ሶስትና አራት አመታት ስፔሻሊቲ ቡና ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች የሚልኩት መጠንና የላኪዎቹም ብዛት እየጨመረ ነው። በፊት ስፔሻሊቲ ቡና አዘጋጅተው ይልኩ የነበሩት። አሁን ግን ከአስር በላይ ላኪዎች ስፔሻሊቲ ኮፊ እያዘጋጁ እየላኩ ናቸው፤ እነዚህ ላኪዎች አርሶ አደሩ ዘንድ ወርደው እየገዙና እያዘጋጁ ይልካሉ።

ለአርሶ አደሩ በጥራት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች መሰጠታቸው በስፔሻሊቲ ቡና ላይ እየታየ ላለው ለውጥ የራሳቸውን ሚና መጫወታቸውን አቶ ታጠቅ ጠቅሰው፣ የካፕ ኦፍ ኤክስለንስ ውድድር መጀመሩም እየተገኘ ላለው ለውጥ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ይናገራሉ። ይህ ማለት በእዚህ አመት በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ እወዳደራለሁ ያለ አርሶ አደር ቡናውን በዚያ ደረጃ ያዘጋጃል ማለት ነው፤ አለፈም ወደቀም ቡናውን በዚያ ደረጃ ለማዘጋጀት ይሰራል ሲሉ ያብራራሉ።

የቀጥታ ግብይት መፈጠሩም የራሱን ሚና ተጫውቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ላኪው ከአቅራቢው ጋር ኮንትራት ሲገባ ደረጃ አንድና ሁለት ብሎ ከተስማማ አቅራቢው አርሶ አደሩን ወደ ማዘዝ ይመጣል፤ ቀዩን ለአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ቡና የሚውል ቡና ይገዛል ማለት ነው፣ የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ መምጣት፣ የግብይት አማራጮች መስፋት፣ ገዢዎች የሚፈልጉት የቡና አይነት እየጨመረ መምጣት ተወደደም ተጠላ የጥራት ደረጃውን እያሳደግን፣ ከኮሜርሻል እየወጣን መጣን ማለት ሲሉ ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ስፔሻሊቲ አንድ ሁለት ሶስት ብለን ብቻ ሳይሆን ከሁለት አመት ወዲህ ደግሞ እየተለመዱ የመጡ የቡና አይነቶች አሉ። ካለፉት ሁለትና ሶስት አመታት ወዲህ የስፔሻሊቲ ቡና ተብለው የሚወሰዱት አነ ሀኒ ኮፊ፣ አናሮቢክና አሮቢክ ኮፊ ፕሮሰስና የመሳሰሉት ፊት ያልተለመዱ በሀገራችን የቡና ዝግጅት ስርአት ውስጥ ያልተካተቱ፣ ቢታወቁም ያልመድናቸውና ያልተካተቱ የቡና ዝግጅት ጥራቶች ናቸው። እነዚህን የቡና ጥራቶች አንዳንድ ላኪዎች ከአርሶ አደሮች ጋር በመሆን እያዘጋጁ መምጣታቸውም እንዲሁ የስፔሻሊቲ ቡና አቅርቦትን እያሳደገው መጥቷል።

ቡናዎቹን ስፔሻሊቲ ከሚያሰኛቸው መካከል አንዱ ዝግጅታቸው ነው፣ ለምሳሌ ከዝግጅታቸው ውስጥ ቀይ ቀዩን ብቻ ወስዶ በሚገባ የበሰለውን ወስዶ በተሻለ የዝግጅት ሂደት እንዲያልፍ፣ በጸሀይ እንዲደርቅ ሲደረግ፣ በአግባቡ ሲጓጓዝ፣ አከመቻቸቱና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ጥራትን ባገናዘበ መልኩ ሲሰሩ የቡናው ጥራት እያደገ ይመጣል። ወሳኙ ጉዳይ ያለው ዝግጅቱ ላይ ነው። ከመልቀም ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ጥራት ላይ መሰረት ያደረገ ስራ ተሰራ ማለት ወደ ስፔሻሊቲ ዝግጅት ውስጥ እንዲመጣ ተደረገ ማለት ነው።

ዳይሬክተሩ ቀደም ሲል ቡና የታጠበ ሲሆን ይፈለጋል፤ አሁንም ብዙ ፈላጊ አለው። በተለይ የታጠበ ስፔሻሊቲ ቡና በብዛት ይፈለጋል ሲሉ ያብራራሉ። አሁን አሁን ደግሞ ቀይ ቀዩን ብቻ በመልቀምና በጸሀይ በማድረቅ የሚቀርብ ስፔሻሊቲ ቡና በጣም ተፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞም ሀኒ ኮፊ ፣ አናሮቢክና የመሳሰሉት በስፔሻሊቲ ዝግጅት ውስጥ የመጡ ናቸው። እነዚህ እየተለመዱ መምጣታቸው ለስፔሻሊቲ ቡና እድገት የራሳቸውን ሚና እንዲጫወቱ ያስችላል ሲሉ ይገልጻሉ።

ቡናን ስፔሻሊቲ ስትለው ነገሮች የሚያያዙት ቀጥታ ከዝግጅት ጋር እንጂ ከቡና አይነት ጋር አይደለም የሚሉት አቶ ታጠቅ፣ ሲዳማ ስትል ሲዳማ ኮሜርሻልም ስፔሻሊቲም አለው ይላሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ቡና ጥራቱን ካልጠበቀ ወደ ኮሜርሻል፣ ጥራቱን ከጠበቀ ደግሞ ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ይሄዳል። ጉዳዩ ቀጥታ የሚገናኘው ከዝግጅት ጋር ነው። ከዘር መረጣ፣ ከተክሉ እንክብካቤ ከቡና አሰባሰብ፣ ከፕሮሰሲንግ ጋር የሚገናኝ ነው።

ኮሜርሻሉ እየቀነሰ ስፔሻሊቲ ቡና እየጨመረ ቢመጣም አሁንም አብዛኛው ወደ ውጭ የሚላከው ቡና ኮሜርሻል ነው የሚሉት ዳይሬክተሩ፣ የለውጡ ጉዞ ግን የቀስ በቀስ መሆኑን ነው የጠቆሙት። ኮሜርሻል ላይ እየሰራ ቆይቶ ባንዴ ወደ ስፔሻሊቲ መሸጋገር እንደማይቻልም ይገልጻሉ። መቶ በመቶ ስፔሻሊቲ ቡና ብታዘጋጅ፣ ለዚያ ገበያ የሚሆን ቡና ላታገኝ ትችላለህ ያሉት አቶ ታጠቅ፣ ስለዚህ በገበያ ላይ በሰራህ፣ እያስተዋወቅህና እየስለመድክ በሄድክ ቁጥር ከኮሜርሻል ወደ ስፔሻሊቲ የበለጠ እየገባህ መምጣት ትችላለህ ሲሉ ያብራራሉ።

ኮሎምቢያ በአብዛኛው ስፔሳሺሊቲ ቡና በመላክ ትታወቃለች፣ ወደውጭ ከምትልከው ቡና አብዛኛውም ስፔሻሊቲ ቡና ነው የሚሉት ዳይሬክተሩ፣ ኮሎምቢያውያን ወደ እዚህ ለመምጣት የሚሄዱበትን መንገድ አስደንጋጭ እንደሆነም ይናገራሉ። እኛ እኮ ቡናችን ራሱ ገበያ እየተፈጠረ እንጂ እኛ እየሰራን አይደለም ነው የሚሉት። ለምሳሌ ኮሎምቢያውያን በእያንዳንዱ የአውሮፓና አሜሪካ ሀገር ቡናቸውን የሚያስተዋወቁባቸውና የሚሸጡባቸው ሱቆች እንዳላቸውም ይናገራሉ።

እንደ አቶ ታጠቅ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በውጭ ሀገሮች ከኤምባሲያችን ውጭ ምንም አይነት ሱቆች የሏትም። ኤምባሲውም ከሰራ ነው፤ ቢዝነስ ኦሬንትድ አይደለም። በእነዚህ ሀገሮች አንድም ሱቅ የላትም። እነሱ በኤዢያ ሀገሮችም ቡናቸውን የሚያስተዋውቁባቸውና የሚሸጡባቸው ሱቆች አሏቸው። ከፍተኛ የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ ነው ስፔሻሊቲ ቡናን በስፋት ለገበያ ማቅረብ የቻሉት።

ሀገርህ ተቀምጠህ፣ ለማስታወቂያ ምንም ገንዘብ ሳታወጣ እንዴት በዓለም ገበያ ከቡና ተጠቃሚ ልትሆን ትችላለህ ሲሉም ይጠይቃሉ። አቶ ታጠቅ በሀገራችን ለቡና ፕሮሞሽን ምንም በጀት እንደሌለም ነው የጠቆሙት። በዚህ ዘመን አንድ ኩባንያ ምንም የማስተዋወቅ ስራ አልሰራም ሲባል መሸጥ አይችልም ወደሚል ደረጃ ይወስዳል ሲሉ አቶ ታጠቅ ይገልጻሉ። የተሻለ ጥራት ያለው ምርት ቢኖርህም፣ እስካላስተዋወቅህ ድረስ ምርትህን ቀርቶ ሀገርህንም የማያውቁ አሉ ያሉት አቶ ታጠቅ፣ በእንደዚህ አይነት ነገሮች ላይ በሰፊው መስራት ይጠበቅብናል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ዳይሬክተሩ በሀገሪቱ የኤክስፖርት ፕሮሞሽን ተቋምም፤ የኤክስፖርት ፕሮሞሽን ስትራቴጂም እንደሌለም ነው የጠቆሙት። ለእዚህም እያንዳንዱን ተቋም መመልከት ይቻላል። እንደ ሀገርም የኤክስፖርት ፕሮሞሽን ስትራቴጂ ለግብርና ምርታችንም ለኢንዱስትሪ ምርታችንም የለም ሲሉ ያመለክታሉ።

በ2014 ዓ.ም ላይ የኤክስፖርት ፕሮሞሽን ስትራቴጂ ሰነድ እየተዘጋጀ እንደነበረም አስታውሰው፣ ፕሮሞሽን ስትራቴጂው ባለፈው በጀት አመት እየተጠናቀቀ መሆኑን አውቃለሁ ይላሉ። እንደ ኮሎምቢያና ብራዚልና ቤትናም ሌሎች ሀገሮች ላይ ፕሮሞት የሚያደርጉ ኮፊ ሀውሶችና እደረጃጀቶች ባይኖሩንም በኢግዚቢሽንና ባዛሮች ላይ የመሳተፍ፣ የተለያዩ የፕሮሞሽን ዘመቻዎችን የመጠቀም፣ ፕላትፎርሞችን የማዘጋጀት እቅዶች አሉን ብለዋል።

እነዚህም ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚጠይቁ ጠቅሰው፣ የፕሮሞሽን ስራ ከገበያ ባለድርሻዎች፣ ከፕሮሞሽን አካላት ጋር የሚሰራ መሆኑን ይናገራሉ። ተቋሙ ብቻውን የሚሰራው አይደለም፤ በተለይ ከባለሀብት አደረጃጀት ማህበራት ጋር በቅንጅት የምንሰራቸው ይሆናሉ። የምንተውው አይሆንም። ቡና ላይ ፤እንደሚሰሩ ቡና አምራች ሀገሮች የተጠናከረ ስራ አይኖረንም እንጂ እንሰራለን ሲሉ ገልጸዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## አንጀት አርስ የፖሊስ ጥበብ

**ዋስልኝ ስዩስ**

የብዙዎችን አንጀት ሲያቃጥል የነበረ ሌባ ወይም ወንጀለኛ ሲያዝ የብዙዎችን አንጀት ያርሳል። አንጀት የሚያርሰው ደግሞ አስደማሚው የፖሊስ ጥበብ ነው። ሙያቸውን በጥቅም በሚሸጡ የሙያ ከሃዲዎችና በስንፍና ሙያውን ባስደፈሩ አንዳንድ ምግባረ ብልሹ ፖሊሶች ወቀሳዎች ቢኖሩም፤ እያወራን ያለነው ግን ለሙያቸውና ቃል ኪዳናቸው ታማኝ ስለሆኑት ፖሊሶች ነው።

ለዚህ ሀሳብ መነሻ የሆነኝ ባለፈው ሳምንት ከአዲስ አበባ ታግቶ ተወስዶ በፖሊስ የክትትል ጥበብ የተገኘው የሕጻን ሳሙኤል ዮሐንስ ዜና ነው።

ይህን ዜና እንዳየሁ ትዝ ያለኝ ከ12 ዓመታት በፊት (2003 ዓ.ም) ባደኩበት አካባቢ የተፈጸመ አንድ የፖሊስ ጥበብ ነው። ያ የፖሊስ ጥበብ ዛሬ ድረስ በአካባቢያችን ሰዎች የሚታወስ ነው፤ ለብዙዎች ማስተማሪያ የሆነ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው።

ከአካባቢያችን አንድ ወጣት ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ይመጣል። የቀን ሥራ ሲሰራ ቆይቶ አንድ ቋሚ ሥራ ያገኛል። በአንድ የጤና ተቋም ውስጥ በጥበቃ ሰራተኝነት ተቀጠረ። ከቆይታ በኋላ በታማኝነት የተሰጠውን ኃላፊነት በህሊና ቢስነት ወደ ጎን ትቶ መዝረፍ አማረው። የሥራ መደቦቹን ለጊዜው እርግጠኛ ባልሆንም ከጥበቃ ሰራተኝነት በኋላ ካርድ ክፍል መግባት እንደቻለ ታሪኩን የሚያውቁ ሲያወሩ ሰምቻለሁ። እስከ 8ኛ ክፍል የትምህርት ማስረጃ ስላለው ከዛሬ 12 ዓመት በፊት ካርድ ክፍል ለመቀጠር በቂ ነው።

ልጁ 12 ሺህ ብር እና ቁሳቁስ ሰርቆ ተሰወረ። ለሕይወት ዘመኑ የሚበቃ ገንዘብ ያገኘ ስለመሰለው ወደ ትውልድ አካባቢው ሄደ። የትውልድ አካባቢውን መልከዓ ምድር እንኳን የአዲስ አበባ ፖሊስ የወረዳው ፖሊሶች እንኳን አያውቁትም።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ሥራውን መሥራት ጀመረ። የተጠቀሙትን ዘዴ እዚህ ላይ ለመዘርዘር ቦታ አይበቃም፤ የተጠቀሙትን ተጠቅመው ልጁ የተወለደበትን ወረዳ ዋና ከተማ አወቁ። በቀጥታ ከአዲስ 220 ኪሎ ሜትር ወደ ደራ ጉንደ መስቀል ገሰገሱ። እዚያ እንደደረሱ ከወረዳው ፖሊሶች ጋር ተገናኙ። ፖሊሳዊ መረጃዎችን ከተለዋወጡ በኋላ ልጁ ከሚኖርበት ቀበሌ ሊቀመንበር ጋር እንዲያገናኟቸው አደረጉ።

በነገራችን ላይ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚደረጉት በጥንቃቄ ነው። አካባቢው ገጠራማ ስለሆነ መረጃው ከተሰማ ልጁ ይሰወራል። ሁሉንም ነገር በምሥጢር ከጨረሱ በኋላ የፖሊስ ልብሳቸውን ቀይረው በሲቪል መንቀሳቀስ ጀመሩ። ልጁ ያለበት ቀበሌ ሲደርሱም ያገኙትን ሰው ሁሉ ይጠይቁ የነበረው ፖሊስ መሆናቸውን ሳይገልጹ መንገድ የጠፋባቸው መንገደኛ መስለው ነው።

ዝርዝሩ ይቅርና እንዲህ እንዲህ እያሉ ቀጥታ ያለበት ቤት ውስጥ ነው የገቡ። ሰላምታ ከተጨባበጡ በኋላ ነው በእጁ ካቴና የገባው። እጁን በካቴና አስረው ተወልዶ ባደገበት አካባቢ አገር ምድሩ እያየው ሌብነቱን ላገኙት ሁሉ እየተናገሩ ተወሰደ።

ፖሊሶቹ ለአካባቢው ሰዎች ሲነግሯቸው፤ ልጁን ለመያዝ የወጣው ወጪ እና የጠፋው ጊዜ ልጁ ከሰረቀው ገንዘብ ጋር ሲነፃፀር በፍፁም አይገናኝም። ከ12 ሺህ በላይ ገንዘብ ወጥቷል፤ ከአንድ ወር በላይ ጊዜ ወስዷል። «ይህን ያደረግነው ወጪው እንደሚበልጥ ስተነው አይደለም፤ እንዲህ አይነት ሌባ ከእኛ ማምለጥ እንደማይችል ለማሳየት ነው» እያሏቸው ነበር።

እንግዲህ ለዚያች ትንሽ ጥፋት (በእርግጥ የስርቆት ትንሽ የለውም) ፖሊስ ያን ያህል ድካም ደክሟል፤ ያን ያህል የኦፕሬሽን ሥራ ተሰርቷል። ለምን ቢሉ! ክህደት ፈጽሟል፤ በአደራ የተሰጠውን ንብረት ዘርፏል። ነገ ከነገ ወዲያ እንደዚያ አይነት ድርጊት እንዳይፈጸም ያደርጋል። እንደተባለውም እነሆ ከዚያ አካባቢ ተመሳሳይ ድርጊት ሰምቼ አላውቅም። ዛሬ ድረስ ያስታውሱታል።

ከፖሊስ ጥፋተኛን የመቅጣት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያስገርመኝ የሚጠቀሙት ጥበብ ነው። እስኪ አሁን ደግሞ አንድ የትራፊክ ፖሊስ ጥበብ ልንገራችሁ።

2009 ዓ.ም ነው። ከደራ ወደ አዲስ አበባ እየመጣሁ ነው። በዚህ መስመር የሚመጣ መኪና የሚጭነው ሰው የአዲስ አበባን አንበሳ ባስ መስሎ ነው። በዚያ ላይ ከታሪፍ በላይ (እጥፍ የሚሆንበት ጊዜም አለ) ነው የሚያስከፍሉ። ለተጓዦቹ ትራፊክ ሲጠይቅ ይህን ያህል ነው የከፈልን ብላችሁ ንገሯቸው ብለው መደበኛውን እንድትናገሩ ያደርጓቸዋል፤ አለበለዚያ መንገድ ላይ እንደሚያወርዷቸው ያስፈሯሯቸዋል።

በዚህም ምክንያት መንገደኛው ሲጠየቅ የሚናገረው መደበኛውን ታሪፍ ነው። እኔ የምጓዝ ዕለት ረዳቱ የተለመደውን መልዕክት አስተላለፈ። በነገራችን ላይ አንዱ ደፍሮ ቢናገርም ትራፊክ ፖሊሶች ስለማይቀጧቸው ምን አዳረቀኝ ብሎ ነው ዝም የሚል። የዚህን ዕለት የገባው ፖሊስ ግን የቆረጠ ይመስላል።

ቀጥታ ወደ መኪናው ውስጥ ገባ። ከፊቱ ያሉትን ሲያይ የተማሩ የሚመስሉ፣ ከተማ ቀመስ ናቸው። እነዚህን ሰዎች ቢጠይቃቸው እንደሚዋሹት ገብቶታል፤ ምክንያቱም ወንበር እንዲያዝላቸው ከረዳቶና ሾፌሮች ጋር የሚሞዳሞዱ ናቸው።

በቀጥታ አይኑ ያማተረው ወደኋላ ነው። አንዲት ነጭ ሻሽ ያደረጉ መነኩሴ እናት አየ። ረዳቱንም ተጓዡንም እያዋዛ እየቀለደ መነኩሴዋ ጋ ሄደ። አጠገባቸው ቁጭ ብሎ «ጉዞ እንዴት ነበር?» እያለ ትንሽ አወራና ስንት እንደከፈሉ ጠየቃቸው። መነኩሴዋ እቅጩን ተናገሩ። ሾፌሩን ጎትቶ አውርዶ ተገቢውን ቅጣት ሰጠው ማለት ነው!

እዚያ ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ አንጀቱ ራሰ። ተጓዡ ከዚያ በፊት ተሰላችቶ የነበረው ትራፊኮች በሩ ላይ ብቅ ብለው ምልስ ሲሉ ነበር። ቢናገሩም በኋላ ከረዳቱ ጋር መሰዳደብ ይሆናል እንጂ አይቀጧቸውም ነበር። ያ ፖሊስ በዚያ መንገድ ሰርቶ ሲሄድ ግን አንጀታቸው ራሰ።

እንዲህ አይነት የፖሊስ ሥራዎች አንጀት አርስ ናቸው። እንዲህ አይነት ሥራዎችን ለመሥራት ደግሞ የራሳቸው ጥበብ አላቸው።

ይህ ይሆን ዘንድ ታዲያ ሕብረተሰቡ ተባባሪ ሊሆን ይገባል። «ፖሊስና ሕብረተሰብ» የሚለው ፕሮግራም ስሙ ገላጭ ነው። ፖሊስ እንዲህ አይነት ሥራዎችን መሥራት የሚችለው ሕብረተሰቡ ወንጀል ተፀያፊ ከሆነ ነው። ለምሳሌ ከላይ የገለጽኩትን የትራፊክ ፖሊሱን ዘዴ መጠቀም ያስፈለገው አስመሳዮች ስለሆንን እንጂ እዚያ መኪና ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ ሊያጋልጥ ይገባ ነበር። ግን እኛም አስመሳዮች ነን፤ አንዳንድ ፖሊሶችም አሳፋሪዎች ናቸው። ቢጠቁሟቸውም በቸልተኝነት ይተውትና ከባለጉዳዩ ጋር መጣላት ይሆናል።

ከምንም በላይ ግን በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ችግር ጥፋተኛን የመደበቅ አባዜ ነው። ፖሊስ ደግሞ ከሕብረተሰቡ በሚያገኘው መረጃ እና በራሱ የምርመራ ጥበብ እንጂ በጥንቆላ አይደለም የሚሰራ። ሕብረተሰቡ ጥፋተኛን ከደበቀ ለጊዜው የረቀቀ ቴክኖሎጂ ስለሌለን ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ ሌባን እና ወንጀለኛን መከላከል የምንችለው ከፖሊስ ጋር በመሆን ነው።

በተለይ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረው ፋሽን የሕጻናት እገታ ነው። ይህን ነገር ከወዲሁ የሕብረተሰብ ርብርብ ካልተደረገበት አደጋው የከፋ ነው። ነገ የሁላችንንም ቤት ያንኳኳል። ስለዚህ እንዲህ አይነቱን አረመኔያዊ ድርጊት ማስቀረት የሁላችንም የዛሬ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል!

# ዓለም አቀፍ

## ኮንጎውያን የሩዋንዳ ጣልቃገብነትን አወገዙ



**ህዝቡ በጎዳና ላይ ተቃውሞውን ሲገልጽ**

በሺዎች የሚቆጠሩ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ነዋሪዎች ሩዋንዳ በኮንጎ የሚንቀሳቀሰዉን ኤም 23/ M25 የሚባለዉ አማፂዉ ቡድን ትደግፋለች በጎማ ከተማ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸዉን አልጀዚራ አስነብቧል፡፡

አማፂያኑ በአሁኑ ጊዜ በተለይ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ገጠራማ አካባቢዎችን በስፋት መቆጣጠሩ ጀርባ የሩዋንዳ ድጋፍ መኖሩ የአገሪቱ ዜጎች ያስቆጣ ድርጊት መሆኑ ተገልጿል።

በስፋት የቱትሲ ጎሳ አባላት መሆኑ የሚነገረዉ ይሄዉ ሸማቂ ቡድን ለዓመታት ጥቃት ሳያደርስ የቆየዉ ቢሆንም የኮንጎ መንግስት እ.ኤ.አ. በ2021 መገባደጃ አካባቢ ተዋጊዎቹን ለአገሪቱ ስጋት መሆናቸዉን በመገንዘብ ወደ ጦር ሰራዊት ለማዋሃድ የስምምነት ሙከራ አልተሳካለትም።

በሰልፉ ላይ የተገኙት የሲቪል ማህበረሰብ ተወካይ የሆኑት ማምቦ ካዋያ “የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ግብዝነት እናወግዛለን” ሲሉ ለኤ ኤፍ ፒ የዜና ወኪል መናገራቸዉም ተነግሯል።

በሩዋንዳ በሚደረግለት ድጋፍ ቡድኑ በአሁኑ ጊዜ የመካከለኛ አፍሪካ ቀጠናዊ ትስስር አደጋ ላይ መጣሉን ማምቦ ካዋያ አክለዉ ገልጸዋል፡፡

በአገሪቱ የጸጥታ አካላትና በኤም 23 መካከል የሚደረግ የተኩስ ልውውጥ ለበርካታ ሳምንታት የቆመ ቢመስልም በተያዘዉ ዓመት ከጥቅምት ወር ጀምሮ ግን ግጭቱ እንደ አዲስ ተባብሶ የቀጠለ ሲሆን በተለይ አማፂያኑ በሰሜናዊ የኪቩ ግዛቶችን በስፋት መቆጣጠራቸዉ እየተነገረ ነዉ፡፡

በተጨማሪም አማፂያኑ በሩዋንዳ ድንበር አቅራቢያ በምትገኘዉና ወደ ጎማ ዋና ከተማ የሚወስደዉን የኪዋንጃ እና ሩትሹሩ ከተሞች ወሳኙ አዉራ ጎዳናን ተቆጣጥሯል።


ባሳለፍነዉ እሁድ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግስት በአገሪቱ የሩዋንዳ አምባሳደር ቪንሰንት ካሬጋ በ48 ሰዓታት ዉስጥ ኮንጎን እንዲለቁ ማዘዛቸዉ ይታወሳል። ሩዋንዳም ጉዳዩን አስመልክታ “ጸጸት የሚያስከትል ውሳኔ “ በማለት ማሳሰቢያ ሰጥታለች፡፡

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሩዋንዳ አዲስ የተሾሙት የአገራቸዉ አምባሳደር የሹመት ደብዳቤ በሩዋንዳ እንዳ መዘገቡ ማዘዛቸዉን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል።

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ይህን ይበል እንጂ የሩዋንዳ መንግስት በበኩሉ ኮንጎ በሁለቱ አገራት መካከል የተፈጠሩ ዉንጀላዎችን በማባባስ ላይ መሆኗን ገልጻ፣ በድንበር አካባቢ ያሉ ወታደሮቿ በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸዉን ጠቁማለች፡፡

በጥቅሉ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ የተረጋጋ አገር እንዳትሆን ሩዋንዳ ለኤም 23 አማፂያን ቡድን ድጋፍ እንደምታደርግ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጭምር በበራሪ ጽሑፎቹ ማረጋገጡን አልጀዚራ በዘገባዉ አመላክቷል፡፡

## የአሜሪካ አፈ ጉባኤዋ የናንሲ ፔሎሲ ባለቤት ጥቃት ተፈፀመባቸው




**ናንሲ ፔሎሲ እና ባለቤታቸው**

የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የናንሲ ፔሎሲ ባለቤት በቤታቸዉ ዉስጥ በመዶሻ ጥቃት እንደተፈጸመባቸው ቢቢሲ አስነብቧል። ናንሲ ፔሎሲ ድርጊቱ እንደተደናገጡና ሐዘን እንደተሰማቸው ገልጸዋል።

ፔሎሲ ጥቃቱ ካጋጠመ በኋላ ሕግ አስከባሪ አካላት በወሰዱት ፈጣን እርምጃ እና ለባለቤታቸው እየተደረገ ባለው የሕክምና ድጋፍ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ዓርብ ጥቅምት 18/2015 ዓ.ም አንድ ጥቃት አድራሻ ግለሰብ ሳን ፍራንሲስኮ ውስጥ ወደ ሚገኘው የአፈ ጉባኤዋ እና ባለቤታቸው መኖሪያ ቤት ዘልቆ በመግባት የ82 ዓመቱ ጎልማሳ ፖል ፔሎሲን በመዶሻ መምታቱንና ፖል ከደረሰባቸው ጉዳት እያገገሙ መሆኑን ናንሲ ፔሎሲ ገልጸዋል።

ፖል ፔሎሲ በደረሰባቸው ጉዳት በራስ ቅላቸው እና ቀኝ እጃቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፣ በሆስፒታል “ሕይወት አድን” ሕክምናቸውን እየተከታተሉ እንደሆነ አፈ ጉባኤዋ ተናግረዋል።

ጥቃቱን በማድረስ ተጠርጥሮ በቁጥጥር ሥር የዋለው የ42 ዓመቱ ዴቪድ ዴፓፕ ወደ ጥንዶቹ መኖሪያ ቤት ዘልቆ ከገባ በኋላ ናንሲ ፔሎሲን የት እንዳሉ መጠየቁ ተዘግቧል።

ጥቃት ሲፈጸም በመኖሪያ ቤታቸው ያልነበሩት ናንሲ፤ ባለቤታቸው ላይ ጉዳት መድረሱ ከተሰማ በኋላ ወደ ሆስፒታል አቅንተዋል።

ፖሊስ እንዳለው ጥቆማ ደርሶት በመኖሪያ ቤቱ ሲደርስ ተጠርጣሪው እና ፖል ፔሎሲ መዶሻውን ለመያዝ ትግል ላይ ነበሩ።

ፖሊስ ጥቃት አድራሹን በመጣል በቁጥጥር ሥር አውሎታል። ግለሰቡ ናንሲ ፔሎሲ ወደ መኖሪያ ቤታቸው እስኪመለሱ ድረስ ፖል ፔሎሲን አስሮ ለማቆየት ሞክሮ እንደነበረም ምንጮች ለሲቢኤስ ኒውስ ተናግረዋል።

ተጠርጣሪው፤ “ናንሲ የት ነች?” እያለ ሲጮህ ነበር ተብሏል። በቁጥጥር ሥር የዋለው የ42 ዓመቱ ጎልማሳ ጥቃት በማድረስ፣ መኖሪያ ቤት ሰበራን ጨምሮ በርካታ ክሶች ይጠብቁታል።

የ82 ዓመቷ ናንሲ ፔሎሲ በአሜሪካ ፖለቲካ ውስጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ከሆኑ ግለሰቦች መካከል አንዷ ናቸው። ፔሎሲ ከምክትል ፕሬዚዳንት ካማላ ሃሪስ በመቀጠል ለአሜሪካ የፕሬዚዳንትነት ሥልጣን ሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

# ባለውለታዎቻችን

# ሰማዕታቱ - ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም

- **“ጥቅምት 24 የተጨፈጨፈው ሰራዊቱ ብቻ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ጭምር ነው።”**

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

ግርማ መንግሥቴ

ወገኖቹን አምኖ አብሯቸው በኖረ፣
ከማሳቸው ውሎ ከአውዳቸው ባደረ፤
እኮ ምን አጥፍቶ በክህደት ተቀጣ፣
ወንድሜ ባለው እጅ ውድ ሕይወቱን አጣ!!

በማለት በወቅቱ በቲውተር ገፃቸው ላይ ሀዘናቸውን ባሰፈሩት በእዮብ ሱራፌል ግጥም እንጀምር።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ ታሪካዊ ቀናት አሉ። ሁሉም የየራሳቸው ታሪክና ገድል ያላቸው ሲሆን አብዛኞቹ የድል ዜና ነጋሪዎች ናቸው። ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ግን ያለ ምንም ተወዳዳሪ በአገራችን ታሪክ ውስጥ የአገር ክህደት የተፈፀመበት፣ የእናት ጡት የተነከሰበት፣ አረመኔያዊ ተግባር የተከናወነበት፣...፤ በአጠቃላይ ሊገለፅ በሚያስችግር ሁኔታ ወንድም ወንድሙ ላይ ሰይፍ የመዘዘበትና ኢሰብአዊ ተግባር የፈፀመበት እለት ነው። ሁኔታውንም፣ በወቅቱ ኢትዮጵያን ለ27 አመታት ሲያስተዳድር ቆይቶ ተመልሶ ወደ ደደቢት የገባው ሕወሓት ቃል አቀባይ፣ በብአዴን አባልነቱና በሕወሓት ደጋፊነቱ የሚታወቀው፣ ሳይውል ሳያድር የእጁን ያገኘው ሴኩቱሬ ጌታቸው ቡድኑ ለ20 ዓመታት በትግራይ ክልልና በድንበር ላይ በነበረው የሰሜን እዝ ሠራዊት ላይ የፈፀመውን ጥቃት (ከትግራይ ቴሌቪዥን ጋር በነበረው ቆይታ) “መብረቃዊ ጥቃት” ማለቱ ብቻ ሳይሆን፤

“ትግራይን ለማንበርከክ በሁሉም አቅጣጫ የተሸረበው ሴራ ሊጠናቀቅ መቅረቡን ደርሰንበታል፣ በፍጥነት መወሰን ያስፈልግ ነበር . . . ለዚያም ነው የሰሜን እዝን በፍጥነት በ45 ደቂቃ በመቆጣጠር እርምጃ የተወሰደው” በማለት በገዛ ወንድሞቹ ላይ የተመፃደቀው መቼም ቢሆን የሚረሳ አይደለም።

ይህ እለት፣ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት፣ በወቅቱ እንዴት ተብሎ ተገለጸ፣ እንዴትስ ሆኖ አለፈ? የሚለውን ወደ ኋላ ሄድ ብሎ ማስታወስ ይግድ ይሆናል። ለመልሱም ከፈረሱ አፍ እንዲሉ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በላይ የለምና ሙሉ ቃላቸው (የጥቃቱን 1ኛ ዓመት በማስመልከት ያስተላለፉት መልእክት) የሚከተለውን ይመስላል።

ክብር ኢትዮጵያን ሲሉ ለተሰው ጀግኖቻችን!!

ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር ናት። ልባም ልጆችዋ አጥር ሆነው የጋረዷት፣ ዋጋ ከፍለው ያደመቋት፣ ተቆጥሮ በማያልቅ መስዋዕትነት ታፍራና ተከብራ የኖረች ሀገር ናት። የሩቁ ቢዘነጋን እንኳን፣ አምና ጥቅምት 24 ግፍ የተፈጸመባቸው ጀግኖቻችን ታሪክ ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም። እያንዳንዳችን የጀግኖቹ ዕዳ አለብን። ዛሬ የቆምነው ለእኛ ሲሉ የግፍ ጽዋን በተጎነጩ ጀግኖቻችን አጥንት ላይ ነው። እነዚያ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች “ከወገኔ በፊት እኔ ልቅደም” ብለው ደማቸውን ለአፈር፣ ሥጋቸውን ለአሞራ ባይሰጡ ኖሮ የዛሬው ቀን ዛሬን ባልመሰለ ነበር።

የሰሜን ዕዝ ሠራዊት የተደራጀው ከአንድ አካባቢ አልነበረም። አማራና ኦሮሞው፣ ሲዳማና ወላይታው፣ አፋርና ጋምቤላው፣ ጉራጌና ሐድያው ከሁሉም ብሔር ተውጣጥቶ ሀገር እንዲጠብቅ የተደራጀ ሠራዊት ነበር። ሀገሬን ብሎ ለሃያ ዓመታት ከቤቱና ካሳደገው ቀዬ ተነጥሎ ዱር እያደረ ድንበር ሲጠብቅ ኖሯል። ሠራዊቱ ለትግራይ ክልልና ለሕዝቡ ከደግነት ውጭ ክፉ ሆኖ አያውቅም። ጠላት ሲመጣ የሚመክት፣ አዝመራ ሲደርስ የሚያጭድ፣ በማኅበረሰባዊ ተግባራት ላይ የሚካፈል ነበር። በደምና በላቡ ለከፈለው ደግነት በምላሹ ከሽብር ቡድኑ ሕወሓት የተቀበለው ክህደት ነው።

ኢትዮጵያን ለመውረር የመጡ ጠላቶች እንደ ሽብር ቡድኑ ዋነኛ የጦር ቤዞችን በመደብደብ አልጀመሩም። ዋና ዋና መኮንኖችን በመግደልና ከባድ መሣሪያዎቻችንን ዘርፈው አልተነሡም። የጦርነት ቅዱስ ባይኖርም ለጭካኔም ልክ አለው። በሽብር ቡድኑ ልክ ኢትዮጵያ ላይ የጨከነ የለም።

ጥቅምት 24 ምሽት ሠራዊቱ ላይ የክህደት ጥቃት ሲፈጸም የሞቱት እነዚያ ጀግኖች ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ እንደመሆናቸው የተፈጸመባቸው ግፍ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመ ግፍ ነው።

የሽብር ቡድኑ በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት መሣሪያ ለመዝረፍ ብቻ የተደረገ ተራ ጥቃት አልነበረም። በተንኮል የተቀመመና በክፋት የተሞላ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። የገዛ ጓዶቹን አስኮብልሎ በተኛበት ከመግደል ባለፈ ከሬሳው ላይ ልብሱን ገፍፎ የአውሬ ቀለብ እንዲሆን እርቃኑን ሜዳ ላይ ጥሎታል። ይኼን ሲያደርግ የሽብር ቡድኑ ዓላማ ሁለት ነው። አንደኛ ሠራዊቱ በሐፍረት በትር እየተቀጣ ሞራሉ እንዲላሽቅና የአቅመ ቢስነት ስሜት እንዲሰማው። ሁለተኛ ሠራዊቱ እርስ በእርስ እንዳይተማመንና “ክፉና ደጉን አብረው ከተካፈሉኝ ጓዶቼ እንደዚህ ዓይነት ነውር ዛሬ ከተፈጸመብኝ ነገስ?” ብሎ እንዲጠራጠር ለማድረግ ታስቦ ነበር። ዳሩ ግን ሠራዊቱ እንደተጠበቀው አልሆነም።

የወንድሞቹ ደም በከንቱ መፍሰስ ያንገበገበው ሠራዊት በፍጥነት ራሱን አደራጅቶ በሦስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሽብር ቡድኑ ያደራጀውን ኃይል ወደ በርሃ እንዲበተን ማድረግ ችሏል። የቡድኑን ቁንጮ አመራሮች አብዛኞቹን ይዞ ለሕግ አስረክቧል። የተፈጸመበትን ክህደት በበቀል ሒሳብ ሳይሆን የሕግ ማስከበር መርሕን በተከተለ መንገድ ሲያከናውን ነበር። በጦርነት ውስጥ ለመርሕ መገዛት ቀላል አይደለም።

ሠራዊታችን ባለፉት ዓመታት ከሽብር ቡድኑ ጋር አያሌ ውጊያዎችን ሲያደርግ ብዙ ዋጋ ከፍሏል። በየጦር ውሎው በጀግንነት እየተዋጋ ለእናት ሀገሩ ተሰውቷል። ለሀገርና ለወገን ያለውን አጋርነት በንግግር ሳይሆን በተግባር አሳይቷል። አሁንም በዱር በገደሉ እየተዋደቀ ነው።

ዛሬ ሽብር ቡድኑ የተሰጠውን የጥሞና ጊዜ እንደ እድል ከመጠቀም ይልቅ እንደ ድል ወሰደው። በአማራና በአፋር ክልል በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ የግፍ በትሩን ቀጥሎበታል። የጥፋት አጋሩ ሸኔም በኦሮሚያ ክልል ወለጋ አካባቢ ልዩ ልዩ አደጋዎችን እየጣለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን እረፍት እየነሣ ነው። ሌሎችም የጥፋት ኃይሎች ከውስጥም ከውጭም ወኪሎቻቸውን አስተባብረው በሙሉ አቅማቸው ኢትዮጵያ ላይ መዝመታቸውን ገፍተውበታል።

ሠራዊታችን ብቻውን ተጋፍጦ የድል ዜና እንዲያበስረን መጠበቅም ሞኝነት ነው። ጠላቶቻችን ተባብረው የደቀኑብን አደጋ ሁላችንም ተባብረን ካልመከትነው ድል የማይታሰብ ነው። የጠላቶቻችን ኅብረት ለፕሮፓጋንዳ የተፈበረከ ጉዳይ አይደለም። እውነት ነው። እነዚህ ኃይሎች ዓላማቸው ግልጽ ነው። ብረት ያነሡት ሀገር ለማፍረስ እንጂ ሀገር ለመገንባት አይደለም።

የኢትዮጵያን ስም በክፉ የሚያብጠለጥሉ፣ ነገ የሊቢያና የሶርያን እጣ ሊያስታቅፉን እንዲመቻቸው የፈጠሩት ዘዴ መሆኑን ልናውቅ ይገባል።

ጠላቶቻችን በዚህ ደረጃ ሲተባበሩብን እኛ አንድ የማንሆንበት ምንም ምክንያት የለም። የወንድምና የእኅቶቹ ጥቃት የሚያንገበግበው ሁሉ ጣት ከመጠቆም ወጥቶ ሀገር የማዳን ፍላጎቱን በተግባር መግለጽ አለበት።

ወደፊት ታሪክ ፍርዱን ይሰጣል። ፈሪውም በፈሪነቱ፣ ሴረኛውም በሴረኛነቱ እንደየግብሩ ይመዘገባል። የሽብር ቡድኑን ትውልድ በክህደት ሲያስታውሳቸው እንደሚኖር ግልጽ ነው። በተቃራኒው በግፍ የተሠውት የሰሜን ዕዝ አባላትን ጨምሮ ለሀገር የሚዋደቁ ጀግኖች ስማቸው በወርቅ ይጻፋል ሲሉ ሃሳባቸውን አጠቃለዋል።

አዎ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን መልእክት ነበር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላለፉት። (የዘንድሮውን፣ 2ኛውን አመት ምክንያት የሚያደርገውን መልእክታቸውንም ወይ ዛሬ ማምሻውን፣ ወይም ነገ ይለቅቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።)

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከገለፁት ውጭ በሕወሓት የተከዳው የሰሜን እዝ ሰራዊት ለ21 አመታት በነበረው ቆይታ ያልሰራው ስራ የሌለ ቢሆንም፣ ከ2005 እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ ያለው ብቻ እንኳ ቢታይ በክልሉ 113 ሚሊዮን 102 ሺህ 426 ብር ግምት ያለው የበጎ አድራጎትና የልማት ስራዎችን አከናውኗል።



| ተ/ቁ | የድጋፍ አይነት | የድጋፍ መጠን | በገንዘብ ሲተመን |
|---|---|---|---|
| 01 | በተለያየ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች | 3,057,427 ብር | 3,057,427ብር |
| 02 | ለአቅመ ደካማ ወገኖች | 2,134,800 ብር | -2,134,800ብር |
| 03 | የእርከን ስራ በኪ.ሜ | 549 ኪ.ሜ | 1,694,514 ብር |
| 04 | የተተከለ ችግኝ በቁጥር | 5,493,611 ችግኝ | 47,252,866 ብር |
| 05 | የተሰሩ ትምህርት ቤቶች | 65 ት/ቤት | 5,455,072 ብር |
| 06 | የተሰሩ የአቅመ ደካማ መኖሪያ ቤቶች | 117 ቤት | 2,618,905 ብር |
| 07 | የተሰሩ መንገዶች በኪ.ሜ | 1,013 ኪ.ሜ | 33,768,712 ብር |
| 08 | የታረመና የተሰበሰበ ሰብል በሄክታር | 23,163 ሄክታር | 12,351,018 ብር |
| 09 | የወጣቶችመዝናኛ ማእከላት በቁጥር | 05 መዝናኛ | 4,769,112 ብር |
| | | ጠ/ድምር በገንዘብ | 113,102,426 ብር |

ምንጭ - የሀገር መከላከያ ሰራዊት ድረ-ገጹ

ትህነግ እንግዲህ ይህንን ሁሉ ነው አብሮ የካደው። ነገ ታስቦ ወደሚውለው እለት እንመለስ።

ባለፈው ዓመት ኅዳር ወር የሕወሓት ኃይሎች በሰሜን ዕዝ ላይ የፈፀሙትን ጥቃት ለማሰብ በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በተካሄደው ሥነ ሥርዓት ላይም፤

“የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዕለቱ ተጨፍጭፈዋል። እኛ ዛሬ በሕይወት ያለን፤ እኔም ወታደር ነኝ የምንል የኢትዮጵያ ልጆች፤ ... አገራችንን ለመበተን የተነሱትን ኃይሎች በእጅ የማንል መሆናችንን ... ዳግም ቃል ኪዳን የምንገባበት ዕለት ነው” ማለታቸው ይታወሳል። (ሕወሓት ኃይሎች በፈጸመባቸው ጥቃት ሕይወታቸው ላለፈ የሀገሪቱ ሠራዊት አባላትን ለማሰብ የህሊና ጸሎት እና የሻማ መብራት መርሃ ግብር ተካሂዷል።)

በተመሳሳይ ወቅት የፌዴሬሽን ምክር ቤትም ድርጊቱን “ጥቅምት 24 የክህደት ጥግ የታየበት ዕለት ነበር” በማለት እንደገለፀውም እዚህ ላይ በተያያዥ ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል።

**ያስንበት ሁኔታ**

ዘንድሮ ኢትዮጵያና አሸባሪው ትህነግ ያሉበት ሁኔታ የተገላቢጦሽ ሆኗል። አሁን መከላከያ ሰራዊት በከፈለው መስዋዕትነት የትግራይ ህዝብ ከባርነት ነጻ ሊወጣ ጫፍ ላይ ደርሷል። አምሳ አመታት ለሚጠጋ ጊዜ በሕወሓት ቀንበር ውስጥ ሲማቅቅ የቆየው የትግራይ ህዝብ ብርሃን ሊያይ ጥቂት ጊዜያት ብቻ ቀርተውታል። የመከላከያ ሰራዊቱ መስዋዕትነት የታሰበውን ግብ እንዲያሳካ የትግራይ ሕዝብ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። የመከላከያ ሠራዊቱን በመንከባከብ፣ ስንቅ በማቀበል፣ ስለተደበቁ ጀሌዎችና የጦር መሣሪያዎች መረጃ በመስጠት፣ መንገድ በመምራት እና አካባቢውን በመጠበቅ የትግራይ ሕዝብ ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፏል። ለዚህም መንግሥት ምስጋናውን ያቀርባል።

**ሠራዊቱ ለትግራይ ክልልና ለሕዝቡ ከደግነት ውጭ ክፉ ሆኖ አያውቅም። ጠላት ሲመጣ የሚመክት፣ አዝመራ ሲደርስ የሚያጭድ፣ በማኅበረሰባዊ ተግባራት ላይ የሚካፈል ነበር**

የትግራይ ሕዝብ በራሱ ልጆች እንጂ በማንም ሊተዳደር አይገባም። ፌዴራላዊ ሥርዓቱም ይሄንን አይፈቅድም። ሕወሓትም ይሄንን ያውቃል። ይደብቃል እንጂ። በመሆኑም የትግራይ ሕዝብ የሕወሓትን የምስለኔ ቴአትር፣ በምስለኔነት ሊኖረው ለሕወሓት ትቶ፣ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር የጀመረውን ትብብር እንዲያጠናክር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ፍላጎት ነው።

በወገናቸው ተክደው ሕይወታቸውን ያጡ ወገኖቻችንን፤ በነገው እለትም መስዋእት የሆኑበትን 2ኛ ዓመት እያሰብን፣ የህሊና ፀሎትም እያደረግን “ምን ጊዜም ድል ለመከላከያ ሰራዊታችን!!!” እንላለን።

**ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!!**

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የአንደኛ ሊግ ውድድር የሚደረግባቸው ከተሞች ታውቀዋል

ቦጋለ አበበ

የ2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ ውድድር የሚጀመርበት ቀን በአንድ ሳምንት ሲራዘም ውድድሮቹ የሚካሄዱባቸው ከተሞችም ተለይተዋል፡፡

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስር ከሚደረጉ ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው አንደኛ ሊግ የ2015 ውድድር የሚጀመርበት ቀን ቀደም ብሎ የታወቀ ቢሆንም ክለቦች ከክፍያ እና ከዝግጅት ጊዜ መጥበብ ጋር በተያያዘ ባቀረቡት የይራዘምልን ጥያቄ ስለመራዘሙ ሶከር ኢትዮጵያ ዘግቧል። ኅዳር 3/2015 ዓ.ም እንደሚጀመር ተገልፆ የነበረው ውድድሩ ኅዳር 10/2015 ዓ.ም እንዲጀመር ተወስኗል።

ወደ ሃምሳ አምስት የሚጠጉ ክለቦችን በአምስት ምድቦች ከፍሎ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው ይህ ውድድር የመጀመሪያው ዙር ፉክክሮች የሚከወኑበት አምስት ከተሞችም ተለይተው ታውቀዋል፡፡ በዚህም ሀዋሳ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ደብረማርቆስ፣ አሰላ እና ቢሾፍቱ ከተሞች የመጀመሪያውን ዙር ውድድር ለማስተናገድ መመረጣቸውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መረጃ ያመላክታል፡፡ የምድብ ድልድሉ እና የዕጣ ማውጣት መርሐ-ግብሩ ደግሞ ጥቅምት 29 እንደሚከወን ቀደም ብሎ መገለጹ ይታወሳል፡፡




በተመሳሳይ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስር የሚደረገው የከፍተኛ ሊግ ውድድር ከዘንድሮው ዓመት ጀምሮ በዘመነ መልኩ የተለያዩ መስፈርቶች ወጥተውለት እንደሚደረግ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በዚህ ዓመት ለማድረግ ካሰባቸው ስራዎች መካከል የከፍተኛ ሊግ ውድድርን በዘመነ መልኩ ማካሄድ የሚለው ይጠቀሳል፡፡ ውድድሩ ዘንድሮ ከሦስቱ ምድቦች በድምሩ አስራ አምስት ክለቦች ወደ አንደኛው ሊግ የሚወርዱ ሲሆን ከቀጣዩ ዓመት ጀምሮ ደግሞ በሁለት ምድብ ተከፍሎ የውድድሩን ጥራት ከፍ በማድረግ ለማከናወን መታሰቡንም ከቀናት በፊት መሰማቱ ይታወሳል፡፡ ጨዋታዎች ቀጥታ የኦንላይን ቴሌቪዥን ስርጭትን እንደሚያገኙ የተገለጸ ሲሆን ከፊፋ ፕላስ ጋር በመቀናጀት ሽፋን እንዲያገኝ መታቀዱ ይታወቃል፡፡

ውድድሩ በፊፋ ፕላስ አማካኝነት በሆላንዱ ኢለቨን ሰቨን በተሰኘ ካምፓኒ አማካኝነት ስርጭቱ የሚተላለፍ ሲሆን ለስርጭቱም ጥራት ያለው ሜዳ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፌዴሬሽኑ ሦስት ሜዳዎችን እንደለየ የሶከር ኢትዮጵያ መረጃ ያመለክታል። ለዚህም የሆሳዕናው አቢዩ ኤርሳሞ ስታዲየም፣ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ እና የባህር ዳር ስታዲየም ውድድሩ እንዲካሄድባቸው ሲወሰን አንድ ተጨማሪ ሜዳንም ለማካተት የጥራት ጉዳይ እየታየ እንደሚገኝ ተጠቁሟል።

እንደ ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የዲኤስቲቪ ስርጭት ሁሉ የከፍተኛ ሊግ ክለቦችም ቀደም ብለው ለቀጥታ ስርጭቱ እንዲመች የክለባቸውን ታሪክ በአግባቡ ሰድረው ማቅረብ እንዳለባቸው እንዲሁም ደግሞ ከትጥቅ አጠቃቀም ማለትም የመለያ፣ ቁምጣ እና የካሶቶኒ አጠቃቀማቸው ሳይዘበራረቅ ወጥነት ያለው ተመሳሳይ ይዘትን የተላበሰ ሆኖ ለውድድሩ መቅረብ እንደሚገባቸውም በግልፅ በመመሪያ መልክ ለክለቦች ተቀምጦላቸዋል፡፡ በተለይ ክለቦች ወጥነት ያለውን ትጥቅን መጠቀማቸው ከማርኬቲንግ ተጠቃሚነት ጋር ተያይዞ በገቢ ራሳቸው ለማሳደግ ወሳኝ በመሆኑ በጥብቅ ትኩረት እንዲሰጡትም ስለ መገለፁ በዘገባው ተጠቁሟል።

## ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በጦርነት ያልተበገረው አምራችነት

ዮሐንስ ምሳው
ከፍተኛ የኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ

የአንድን አገር ህልውና በዘላቂነት ለማረጋገጥ በኢኮኖሚና በዲፕሎማሲ ስራው ጠንካራ መሆን ያስፈልጋል። ጦርነት ባለመኖሩ ብቻ ሰላም አለ! ማለት አይቻልም። ሰላም የውስጥና የመንፈስ ደስታና እርካታም ነው። ሰላም ለራስና ለሌሎችም ሰዎች ሙሉ አክብሮት ሲኖር ነው። ሰላም በራስና በሌሎች ሰዎች መካከል መተማመን ሲኖር ነው። ሰላም ባለው ህግና ሥነ ሥርዓት ላይ ሙሉ እምነት ሲኖርና በበጎ መንፈስ የራስን ችሎታ በማዳበር የግል ኑሮን ለመምራት የሚያበቃ ሁኔታ ሲኖር ነው።

በዝምታና በፀጥታ ውስጥም ጦርነት እንዳለ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በገሀድ የወጣ ጦርነት ውድ የሆነውን የሰውን ልጅ ሕይወት ይቀጥፋል በተለይ የአምራቹን ዜጋ፣ እድሜ ልክ የተሰራበትና የተለፋበት ንብረት ያወድማል፣ የአገር እድገት ቁልቁል ያወርዳል፣ የዜጎችን የመኖር ተስፋን ያመነምናል። ጦርነት ይዞት ከሚመጣ ጥሩ ነገር ይልቅ ትቶት የሚሄደው መጥፎ ጠባሳ ያመዝናል።



ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት አገር በቀል አምራች ኢንተርፕራይዞች ከፍተኛ የሆነ አስተዋጾ አላቸው። በማደግ ላይ ያለው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ እንደዚህ አይነት ጦርነት ሲገጥመው በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ያስከትላል። በጦርነት ምክንያት በርካታ አምራች ኢንተርፕራይዞች በተለይም በሦስቱ ክልሎች (በአማራ፣ በአፋርና በትግራይ) የሚገኙ አምራች ኢንተርፕራይዞች የችግሩ ዋነኛ ገፈት ቀማሽ ናቸው። ዘርፉ ከምርት በተጨማሪ የሚፈጥረው የስራ እድል በርካታ ቢሆንም በጦርነቱ ምክንያት የሚፈለገው ደረጃ መድረስ አልተቻለም።

የኢንዱስትሪዎች መጎዳት በአገራችን በርካታ ችግሮች አምጥተዋል ከነዚህም መካከል፤ በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ተበትኖ ለከፋ ችግር ተጋልጧል፣ የተመረቱ ምርቶች ለተገልጋይ ደንበኞቻቸው በወቅቱ ባለመድረሳቸው በተጠቃሚውና በሻጩ መካከል ያለውን መልካም የስራ ግንኙነት አሻክሯል፣ ከፍተኛ ወጭ የወጣባቸው ንብረቶች ወድመዋል፣ የአገር ውስጥ ገበያ እንዳይረጋጋ አድርጓል፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ተፈጥሯል።

መንግስት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተጎዱ አምራች ኢንተርፕራይዞችን መልሶ የማቋቋም ስራዎች እየሰራ ይገኛል። ኢትዮጵያ በጦርነት ውስጥም ሆና የአገር ውስጥ ምርቶችን ኤክስፖርት በማድረግ ከ500 ሚሊየን ዶላር በላይ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ገቢ ማግኘት ችላላች።

አሁን ላይ በግብርናው ዘርፍ በተለይ በስንዴ ምርት ላይ እራስን ከመመገብ ባለፈ ለሌሎች መትረፍ የሚያስችል ጅምር ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ግብርናውን ከኢንዱስትሪው አጣምሮ በዘላቂነት ውጤት ለማምጣት መንግስት በትኩረት እየሰራ ነው። በአገራችን 22ሺ 233 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን እነዚህን በተለያየ አግባቡ በመደገፍ ለፍሬ በማብቃት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል።

ዘርፉን የተሻለ ለማድረግ ከማን ምን ይጠበቃል? የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ማደግ ከፍተኛ አስተዋጾ አለው። በመሆኑም የዚህ ዘርፍ መጎዳት የአገር ኢኮኖሚ አደጋ ውስጥ እንደሚገባ ስለሚጠቁም የሚመለከታቸው አካላት የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል።

በተቋም ደረጃ፡- የዘርፉ አመራርና ባለሙያዎች እንደ ባለሙያ ብቻ ሳይሆን እንደ ዜጋ የዘርፉን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት በመረዳት መሰል ችግሮች እንዳይከሰቱ በሚያስችል መልኩ በላቀ ተነሳሽነት በአገራዊ ኃላፊነት በአገር መውደድ ስሜት በትጋት የተሰጣቸውን ተልዕኮ እንዲፈፅሙ ማድረግ፣ ተቋሙ ያሉትን አቅሞች ሁሉ ለዘርፉ ስኬት እንዲያውል ማድረግ፣ ወቅቱን ታሳቢ ያደረጉና ዘላቂ የሆኑ የድጋፍ ማዕቀፎች፤ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እንዲተገበሩ ማድረግ፣

ከአምራቹ፡- ጦርነት የደረሱ ጉዳቶችን በአግባቡ ለሚመለከተው አካል በማስረዳት የመፍትሄው አካል እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቃል፣ ከነበሩ ችግሮች ተሞክሮ በመውሰድ ቀጣይ እንደዚህ አይነት ችግሮች ቢያጋጥሙ በምን አይነት መልኩ ማለፍና መከላከል እንደሚቻል ትምህርት እንዲወስዱ ማድረግ፣

ከዜጎች፡- ዜጎች የአገር ውስጥ አምራች ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች ከነውስንነቶቻቸውም ቢሆን በመሸመትና ለሌሎች በማስተዋወቅ በአገራቸው ምርት መኩራት መቻል አለባቸው፣ በመጨረሻም የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የተሻለ ደረጃ ለማድረስ ማህበረሰቡ በሚችለው አቅም የበኩሉን ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት የዝግጅት ክፍሉ መልእክቱን ያስተላልፋል።

ቴሌግራም፡t.me/ethiopianenterprisedevelopment

ፌስቡክ፡ www.facebook.com/ethiopianenterprisedevelopment